ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል ልዩ ዕትም 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5፣ ሰኔ 2007

## የመጀመሪያ ምዕራፍ የራዕይ ጥበብ 2017 ጉዟችን

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

"የንባብ ክህሎት ለሁሉም ተግባር እጅግ ጠቃሚ ነው።"

ዶ/ር ፀሀይ ጀምበሩ

ከስኬታማ ተማሪዎች አንደበት

ያልተጠበቀ አጨራረስ

(የገጠመኝ ጽሑፍ)




## Graduates of 2015 Congratulations!




ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በቅደመና በድህረ ምረቃ በመደበኛ፣ በማታ፣በክረምትና በርቀት መርኃ ግብሮች ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች በ2007 ዓ.ም እንሆ አስመረቀ!!!




እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

Congratulations!



ናይል
THE NILE

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility

---


# ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

**የአማካሪ ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
ዶ/ር እንየው ታደሰ
አቶ በላይነህ ወርቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢ**
ሂሩት አድማሱ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው
አለምነሽ ሙሉ

ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

ብራና ማተሚያ ቤት ታተመ


እንኳን ደስ አላችሁ!

## ርዕሰ-አንቀጽ

# ምርቃት የስኬት የመጀመሪያው ምዕራፍ ነው!

ውድ ተመራቂ ተማሪዎች በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቆይታችሁ በበርካታ ጥረትና ውጣ ውረድ የተሞላውን መንገድ አልፋችሁ ዓላማችሁን አሳክታችሁ ለዚህ ምርቃት በመብቃታችሁ በናይል ጋዜጣ ስም እንኳን ደስ አላችሁ እንላለን፡፡ ለዚህ ስኬት ለመድረስ ዋነኛው ተዋንያን እናንተ ብትሆኑም ቤተሰቦቻችሁ፣ ወላጆቻችሁ፣ የቅርብ ዘመዶቻችሁና ወዳጆቻችሁ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ በሙሉ የበኩላቸውን ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ከፍተኛ ስኬት አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እንወዳለን፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን በያዘው ራዕይ ጥበብ 2017 ጉዞ የእናንተ አስተዋጽኦ ጉልህ ድርሻ እንዳለው ይታወቃል፡፡ ይህ ራዕይ የሁላችን ራዕይ ነው፡፡ ከተመረቃችሁ በኋላም ባገኛችሁት እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ሀገሪቱን በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማሕበራዊ፣ በቴክኖሎጂና በባሕል ረገድ ከፍተኛ ዕድገት እንድታመጣ የራሳችሁን ሚና በመወጣት ሀላፊነታችሁን እንድትወጡ ያስችላችኃል፡፡ በፊታችሁ ያለውን ረጅም ጉዞ ለመጨረስ አሁን አንድ እርምጃ ተጉዛችሁ ለስኬት በቅታችኃል፡፡ ጉዞው ግን በበለጠ ስኬት መቀጠል አለበት፡፡

አሁን የያዛችሁት የስኬት መንገድ የመጀመሪያ ምዕራፍ እንጂ የመጨረሻ እንደማይሆን እያንዳንዱ ተመራቂ ማመን አለበት፡፡ በዚህ የመጀመሪያ ምዕራፍ ያገኙናቸውን ጠንካራ ጎኖችን የበለጠ በማጠናከር እንዲሁም የታዩ ክፍተቶችን በማረምና ከደካማ ጐኖች በመማር ለበለጠ ውጤት ጠንክረን የምንሰራበት ሊሆን ይገባል፡፡ ከለበሳችሁት የመመረቂያ ጋዋን በስተጀርባ በርካታ የቤት ሥራዎች ይጠብቃችኃል፡፡ ይህን የቤት ሥራ ለመስራት አቅማችሁ የፈቀደውን ሁሉ መስዕዋትነት በመክፈል በፍጹም ታታሪነት፣ ቁርጠኝነት እና ሙያዊ ብቃት ሀገራዊ ግዴታችሁን እንድትወጡ በዚሁ አጋጣሚ ለማሳሰብ እንፈልጋለን፡፡

ለ2007 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪዎች በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ እንላለን!

## መልዕክት



እንዳስ ቃሶ

የስርዓተ ጾታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የ2007 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪዎች እንኳን ደስ አላችሁ!!!

ዩኒቨርሲቲያችን በየዓመቱ ብዛትና ጥራት ያላቸው ተማሪዎችን በማፍራትና ወደ ህብረተሰቡ በመቀላቀል የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በማብቃት ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሳለፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ሴቶች በትምህርት፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ የራሳቸውን ድርሻ እንዲወስዱ ለማድረግ በየዓመቱ ብዛት ያላቸውን ሴት ተማሪዎች በመቀበልና በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማስቻል በስርዓተ ጾታ ዳይሬክቶሬት አማካኝነት አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ እነሆ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ሴት ተማሪዎች በዘንድሮ ዓመት ያስመርቃል፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በተሻለ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በመቀበልና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በርካታ ድጋፎችን በማድረግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች በዚህ ዓመት ያስመርቃል፡፡

ውድ ተመራቂ ሴት ተማሪዎች እና የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች

በነበራችሁ የዩኒቨርሲቲ ቆይታ ያካበታችሁትን እውቀት እና ክህሎት በመጠቀም የማህበረሰቡን ዘርፈ ብዙ ችግሮች የምትፈቱና በተለይም ለሴት ተማሪዎች እና ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አርአያ በመሆን በፈጣን ጉዞ ላይ የሚገኘውን የሃገራችንን ልማት ለማፋጠን የበኩላችሁን ሀላፊነት እንድትወጡ በስርዓተ ጾታ ዳይሬክቶሬት ስም አደራ እያልኩ በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ፡፡

## ቁልፍ መልዕክት



ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር) - ፕሬዚዳንት

### የመጀመሪያ ምዕራፍ የራዕይ ጥበብ 2017 ጉዟችን

የአስራ አምስት አመቱን የራዕይ ጥበብ 2017 ጉዞ ከጀመርን እነሆ የመጀመሪያውን አምስት አመት አሳለፍን፡፡ በዚህ የራዕዩ የመጀመሪያ ምዕራፍ ጉዟችን ስኬት የዩኒቨርሲቲያችን ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች፣ የቦርድ አባላት፣ የዩኒቨርሲቲያችን አመራሮችና ደጋፊዎች ላደረጋችሁት ንቁ ተሳትፎ ምስጋናችን ይድረሳችሁ፡፡ የራዕይ ጥበብ 2017 ጉዞ በአምስት ምዕራፎች የተከፋፈለና ዩኒቨርሲቲያችን በአፍሪካ ካሉ ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲ አንዱ ለማድረግ በማለም የምንከተለውን መስመር የያዘ ራዕይ ነው፡፡

የዚህ ራዕይ ዋነኛ ቁምነገር ተወዳድሮ የማሸነፍ ሳይሆን በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ ዕድገት እንዲመጣ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ተቋም መመሥረትን ያለመ ነው፡፡ በመሆኑም ስኬቱ የሚመዘነው በማህበረሰባችን ላይ በቀጥታ በሚታዩ ዕድገቶች ላይ ሚናችንን በመፈተሽ ነው፡፡ የምናስተምረው፣ የምንመራመረውና ማሕበረሰብ አገልግሎት የምንሰጠው ተጨባጭ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል እውቀት፣ ክህሎትና አጠቃላይ አመለካከት ለመታጠቅ ነው፡፡ ከዚህ እይታ ውጭ የሆነ ትምህርት ከንቱ ልፋት ከመሆን አይዘልም፡፡

ያጠናቀቅነው የመጀመሪያ ምዕራፍ ለራዕዩ መሳካት መሠረት የጣልንበትና ወዳሰብነው መዳረሻም ብዙ ርቀት የሄድንበት ነበር፡፡ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ዋነኛ መገለጫ ብዛት ያላቸው ተማሪዎችን በ2ኛና በ3ኛ ዲግሪ ማሰልጠን መቻልና በታዋቂ መጽሔቶች ላይ የሚያሳትሙ ምሁራን በርካታ መሆን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ ይህን የመጀመሪያ ምዕራፍ ጉዟችንን ስንጀምር በጣም ጥቂት የ2ኛ ዲግሪ ፕሮግራም ብቻ ከፍተን ከሁለት መቶ የማይበልጡ ተማሪዎች ነበሩን፡፡ በአምስት አመት ጉዟችን በርካታ የ2ኛ ዲግሪ ፕሮግራሞችን ከ10 በላይ የ3ኛ ዲግሪ ፕሮግራሞችን በመክፈት ከአምስት ሺህ በላይ የ2ኛ እና 3ኛ ዲግሪ ተማሪዎች ባለቤት ሆነናል፡፡ ይህ ታላቅ ስኬት ነው፡፡ ሌላው የምርምር ዩኒቨርሲቲ መገለጫ በታወቁ መጽሔቶች የሚያሳትሙ ምሁራን መጨመር ነው፡፡ በዚህም ረገድ ጉዟችንን ስንጀምር በዓመት ከ50 ሕትመት በላይ አይታተምም ነበር፡፡ ከአምስት አመት ጉዞ በኋላ ዩኒቨርሲቲያችን ከ300 ሕትመቶች በላይ የሚያሳትም ተቋም ሆኗል፡፡ በመሆኑም በዚህም መስፈርት እድገታችን በእቅዳችን ልክ ባይሆንም አመርቂ የሚባል ነው፡፡

የምርምር ዩኒቨርሲቲ በመሠረተ ልማት ዘርፍም ይመዘናል፡፡ በዚህ ዘርፍ ግዙፍ የመሰረተ ልማት ሥራዎችን በርካታ ቢሊዮን ብር በመመደብ ባለፉት አመታት መስራታችን ታሪካዊ ስኬታችን ከመሆኑም በላይ ለበርካታ ዜጐች የሥራ እድል ፈጥሯል፡፡ በግንባታው ዘርፍ ብዛትንና ጥራትን አጣምረን የዩኒቨርሲቲያችንን የመወሰንና የመፈጸም አቅም በእጅጉ በማጐልበታችን ያገኘነው ውጤት በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ግቢዎችን ገንብተን ለአገልግሎት ስናበቃ የተወሰኑትን ደግሞ በቅርብ ለማስጀመር እየተረባረብን እንገኛለን፡፡ ከላይ የተገለጹት ስኬቶች እንደተጠበቁ ሆነው ምርምርና ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ማስፋፋትና ማጠናከር ከዚህ በላይ የምንሄድበት እድል እንደነበረ ግልጽ ነው፡፡

የተወደዳችሁ የዩኒቨርሲቲያችን ማሕበረሰብ በሚቀጥለው የራዕይ ጥበብ 2017 ምዕራፍ ከመጀመሪያው ምእራፍ ጠንካራና ደካማ ጐናችን ተምረን በጋራ ላቀድነው ራዕይ ስኬት በመረባረብ አመርቂ ሥራ የምንሠራበት ሊሆን ይገባል፡፡ ትኩረታችን አሁንም የሚሆነው የሰው ሐይል ልማትና ጥራት ያለው መሠረተ ልማት ማሟላት ላይ ይሆናል፡፡ የሰው ሐይል ልማታች የመምህራኖችን፣ የአመራሮቻችንን፣ የቦርድ አባላትንና የድጋፍ ሰጭ ሠራተኞቻችንን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የመገንባትና የማሳደግ ሥራን የያዘ ነው፡፡ ከመሠረተ ልማት አንጻር መኖሪያ የሆኑና ያልሆኑ ህንፃዎች ግንባታ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ የቤተ-ሙከራዎችና ፋብሪካዎችን መመሥረትን የሚያካትት ነው፡፡ በመጨረሻም ሁሉም የዩኒቨርሲቲያችን ማሕበረሰብ በየክፍሉ የዘርፉን የመጀመሪያ ምዕራፍ ጉዞ በሚገባ በመገምገምና ወደፊት የሚጠበቅበትን በማወቅና ግልጽነት በመያዝ ለራዕይ ጥበብ 2017 ስኬት የራሱን ሚና እንዲጫወት ዩኒቨርሲቲያችን ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ኃላፊ ሆነን የማያልፍ ስራ የመስራት ዕድላችንን እንጠቀም፡፡

በመጨረሻም ለ2007 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪዎች በቀየስነው የራዕይ ጥበብ 2017 መንገድ ተጉዛችሁ ለምረቃ ስለበቃችሁ እንኳን ደስ አላችሁ፡፡

ስኬት ለራዕይ ጥበብ 2017!


ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

ፕሬዚዳንት - ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

Congratulations!



# መልዕክት



ማተቤ ታፈረ (ዶ/ር)

የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዘዳንት

## ውድ ተመራቂዎቻችን፡-

በመጀመሪያ ለረጅም ዓመታት በርካታ ጥረት ስታደርጉለት የነበረውን ዓላማችሁን አሳክታችሁ ለዚህ ምርቃት በመብቃታችሁ እንኳን ደስ አላችሁ፡ ፡ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ከናንተ ድካምና ውጣ ውረድ ባሻገር ወላጆቻችሁ፣ እንዲሁም የቅርብ ዘመዶቻችሁና ወዳጆቻችሁ የበኩላቸውን ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳበረከቱ ይሰማኛል፡፡ እናንተም ከቤተሰቦቻችሁና ከወዳጆቻችሁ የተሰጣችሁን ድጋፍ እና አደራ በአግባብ በመገንዘብ እና አላማችሁን ለማሳካት አስፈላጊውን ጥረት በማድረጋችሁ ደስታችሁ ከናንተም አልፎ በዙሪያችሁ ያሉ በርካታ አካላትን ያቀፈ ስለሆነ በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ፡፡

አስቀድሜ ለመግለጽ እንደሞከርኩት የናንተ ለዚህ ስኬት መብቃት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ደስታ እንደሆነ ሁሉ ከመመረቃችሁ ባሻገር በርካታ የቤት ሥራዎች የሚጠብቋችሁ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባችኋል፡፡ በምርቃታችሁ ጊዜ የምትለብሱት ጋዎን ሕዝባችሁን ለማገልገል ቃል-መሃላ እየፈጸማችሁ መሆኑን የምታበስሩበት ምልክት እንደሆነ የሀገራችሁ ህዝብ ይገነዘባል፡፡ ይህን የናንተን መመረቅ በጉጉት የሚጠብቀው ህዝባችሁ በርካታ የቤት ሥራዎችን እንድትሰሩለትም ይጠብቃል፡፡ በመሆኑም ይህን ታላቅ ሀገራዊ አደራ እየተረከባችሁ እንደሆነ በመገንዘብ አቅማችሁ የፈቀደውን ሁሉ መስዕዋትነት በመክፈል የሃገራችሁን ህዳሴ በማረጋገጥ ረገድ ፋና-ወጊ ሆናችሁ ማየት እንፈልጋለን፡፡

የልማትና የዲሞክራሲ ፋና-ወጊዎች ከመሆን አኳያ የአገልጋይነት ስሜትና የሥራ ተነሳሽነት ከውስጥ ማዳበር፡ የልማታዊ ዲሞክራሲና የፍትህ መርሆችን በአግባቡ ማጤን፣ እንዲሁም ተቻችሎና ተግባብቶ በመኖር ብዝሃነት ውበት መሆኑን በአግባቡ መገንዘብ ይገባችኋል፡፡ የልማትና የዲሞክራሲ ፋና ወጊነታችሁን የምታረጋግጡበት ሌላው መንገድ ደግሞ በተማራችሁበት የሙያ ዘርፍ የዘመኑን ሳይንስ ከሃገራችን እና ከአለም አቀፍ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ አስፈላጊውን ትንታኔ ለመስጠት የሚያስችል እውቀትን በየጊዜው ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ለረጅም አመታት ያካበታችሁትን አመለካከትና እውቀት ወደ ተግባር በመቀየር የማሕበረሰባችሁን ቁልፍ ችግሮች ልትፈቱበት የሚያስችላችሁ አስተማማኝ ክህሎት በየጊዜው ማዳበር ይጠበቅባችኋል፡፡ ይህን ማድረግ ከቻላችሁ በእውነትም በምረቃችሁ ቀን የለበሳችሁት ጋዋን የቃል ኪዳን ማብሰሪያችሁ እንደነበር እና የረጅም ዓመታት የጥረት ግባችሁም መመረቅ ብቻ ሳይሆን ህዝባችሁን ማገልገል እንደነበር ማረጋገጥ ችላችኋል ማለት ነው፡፡ በቀጣይ የሥራ ዘመናችሁ መልካሙን ሁሉ እመኝላችኋለሁ፡፡

"ለሃገራችን ህዳሴ ተቀራርበን እና ተግባብተን ለመሥራት በጋራ እንሰለፍ"

ማተቤ ታፈረ (ዶ/ር)

የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት



እያዩ ሞላ ፈጠነ (ደ/ር)

የአስተዳደር ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት

## ውድ ተመራቂዎች:-

ከብዙ ዓመታት ጥረትና ልፋት በኂላ ለዛሬው የምረቃ ዕለት በመብቃታችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እወዳለሁ፡፡ የዛሬው ደስታችሁ እንዲሁ የተገኘ ሳይሆን የቤተሰብ፣ የአገር እና የበርካታ አካላት በነቃ ተሳትፎ ነው፡፡

የባሕርዳር ዮኒቨርሲቲ ከቤተሰቦቻችሁ እናንተን በኃላፊነት ከተረከበ በኂላ በቆይታችሁ ማግኘት የሚገባችሁን እውቀትና ክህሎት ለማስጨበጥና ለናንተ ማድረግ ያለበትን ሁለንተናዊ ድጋፍ ሲያደርግ የነበረ ሲሆን እናንተም ከምረቃ በኂላ በምትሰማሩበት የሥራ መስክ ሁሉ አገራችሁንና ወገናችሁን በፍጹም ታታሪነት፣ ቁርጠኝነት እና ሙያዊ ብቃት እንድታገለግሉ አሳስባለሁ፡፡

የዛሬው ምርቃት ለአብዛኛዎቻችሁ የሕይወታችሁ የመጀመሪያ ምዕራፍ ማጠናቀቂያ እንጂ የሁሉም ነገር መጨረሻ አለመሆኑን አውቃችሁ በምትሰማሩበት ዘርፍ ከዩኒቨርሲቲያችን ያገኛችሁትን እውቀት ከተግባር ጋር በማጣመር በሥራ አለም የሚገጥሟችሁን የሕይወት ተግዳሮቶች በማለፍ በማያቋርጥ የመማር ሂደት ራሳችሁን በማሻሻል ለሌላ የሕይወት ምዕራፍ መዘጋጀት አለባችሁ፡፡

የሀገራችን ኢትዮጵያ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የሚኖረው በገጠሪቱ የሀገሪቱ ክፍል በመሆኑ የሕብረተሰቡን ኑሮ ወደተሻለ ምእራፍ ለማሸጋገር የሚደረገው ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ ውስጥ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታበረክቱ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡ ሀገሪቱን በመሠረታዊነት ለመቀየር ከ2003 እስከ 2007ዓ.ም ባሉት ዓመታት የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ተነድፎ መጠነ ሰፊ ርብርብ ተደርጓል፡፡ በአብዛኛው የተነደፉት የልማት ሥራዎች ወጣቶችን በሰፊው ያሳተፉም ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው አምስት ዓመታት ማጠናቀቂያና የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን መጀመሪያ ወቅት የምትመረቁ ወጣቶች ሀገሪቱ በነደፈቻቸው በርካታ የልማት፣ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን መርኀ ግብሮች በመሳተፍ ታሪካዊ አሻራችሁን የምታሳርፉ ትውልዶች በመሆናችሁ ራሳችሁን ለበለጠ ስኬት ማዘጋጀት ይኖርባችኂል፡፡

ዜጎች ሰርተው የሚያልፉ ሀገር ግን ዘላለማዊ በመሆኗ የወጣትነት አፍላ ጉልበታችሁን በወርቃማ የልማት ሥራዎች ላይ በማዋልና በሥራ ፈጠራ ሀገራችን ካለችበት ደረጃ ከፍ በማድረግ ሂደት እና ከድህነት ለመላቀቅ የምታደርገውን ትንቅንቅ በመደገፍ መሪ ተዋናይ በመሆን ትውልዳዊ አደራችሁን እንድትወጡ እጠይቃለሁ፡፡

በመጨረሻም በዩኒቨርስቲያችን ልዩ ልዩ ክፍሎችን በመደራጀት በቆይታችሁ የተሟላ አገልግሎት አግኝታችሁ ለዚህ ለአሁኑ ደረጃ እንድትበቁ ላደረጉ የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞችን እያመሰገንኩ ተመራቂዎችም በምትሄዱበት ቦታ ሁሉ ለዩኒቨርሲቲው አምባሳደር እንድትሆኑ ጥሪዬን በማስተላለፍ በድጋሚ በራሴና በአስተዳደር ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ስም እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ፡፡

እያዩ ሞላ ፈጠነ (ደ/ር)


የአስተዳደር ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት




እንኳን ደስ አላችሁ!



# መልዕክት



ተስፋዬ ሽፈራው (ዶ/ር)

የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት

ውድ የ2007 ዓ.ም. የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተመራቂ ተማሪዎቻችን እንኳን ደስ አላችሁ!

ከሁሉ አስቀድሜ ከረጅም አመታት የግል ጥረታችሁ የቤተሰብ፣ የጓደኞቻችሁና የመምህሮቻችሁ ድጋፍና ክትትል በኋላ የሕይወታችሁ አንዱና ዋነኛው ምዕራፍ ለሆነው የምርቃት እለታችሁ እንኳን በሰላም አደረሳችሁ፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን ጥራት ያለው ትምህርት ለተማሪዎቻችን በማድረስ ከሳይንሳዊ ትንታኔና ግንዛቤ ጋር ከማስታጠቅ በተጨማሪ ምርምርን በማዳበር የአካባቢያቸውን ችግሮች በመቅረፍ ለማሕበረሰባቸው ደራሽ የሆኑ ምሩቃንን ለማፍራት ራዕይ ጥበብ 2017ን ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ እናንተም አንደኛውን የስትራቴጂክ እቅዳችንን አጠናቀን 2ኛውን የራዕይ ጥበብ 2017ን ስትራቴጂክ እቅዳችንን በምናዘጋጅበት ወቅት ተመራቂ በመሆናችሁና የስኬታችንን ደረጃ የምንለካባችሁ በመሆናችሁ ምረቃችሁን ለየት ያደርገዋል፡፡

እንግዲህ ዛሬ መመረቅ ማለት ከአንደኛው የሕይወት ምዕራፍ ወደ ሌላኛው ስትሸጋገሩ ልዩ አቅምና ችሎታ ይዛችሁ ለመሻገራችሁ የብስራት ሰርተፊኬት የምትወስዱበት በመሆኑ ነገ ለሚጠብቃችሁ ሕይወትም ዝግጁ መሆን ይጠበቅባችኋል፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ እያሳየች ያለውን እድገት ዘላቂና ወጥነት ያለው ሆኖ እንዲቀጥል የዩኒቨርሲቲያችን እድገትና ልማት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ለዚህም ነው የእኛ ዩኒቨርሲቲ "የምርምርና ፈጠራ ተቋም ሆኘ ለሃገሬ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ሀይል ለማፍራት ሃላፊነቴን እወስዳለሁ" ብሎ ራዕይ ጥበብ 2017ን ነድፎ እየሰራ ያለው፡፡ እናንተም ከዚህ ተቋም በመመረቃችሁ በምትሄዱበት ሁሉ የዩኒቨርሲቲያችን አምባሳደር በመሆን ጥራት ያለው የሙያ አገልግሎት በመስጠትና ቀጣይ አቅማችሁን በትምህርት በመገንባት ለዩኒቨርሲቲያችን ራዕይ መሳካት የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታበረክቱ ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ራዕዩን ለማሳካትም ለአካባቢያችንና ለአገራችን ልማትና እድገት መሠረት ይሆናሉ ባላቸው ዘርፎች ላይ በርካታ የምርምር ተቋማትን በማቋቋምና መምህራንን በየተቋማቸው በቡድን በማደራጀት መጠነ ሰፊ የምርምር ሥራዎችን በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ የምርምር ሥራዎችም ከተጠናቀቁ በኋላ በተለያዩ እውቅና ያላቸው የምርምር መድረኮች በተለያዩ የመገናኛ ስልቶች በመጠቀም የዩኒቨርሲቲያችንን የሥራ ውጤት በማስተዋወቅ ከፍተኛ ለውጥ እየመጣ ነው፡፡ በነዚህ ምርምሮች የተገኙ እውቀቶችንም በገጠርና በከተማ በመክፈል ሞዴሎችን በመለየት በማሕበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ በኩል ለማህበረሰቡ ችግር መፍትሄ እንዲሰጡ የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተለይም በትምህርት፣ በጤና፣ በገጠርና ከተማ ግብርና፣ በአገልግሎት አቅም ግንባታና መልካም አስተዳደር ግንባታ ዙሪያ በርካታ ለውጦችን እያመጣን እንገኛለን፡ ፡ ለዚህም ስኬት ተማሪዎቻችን ከመምህራን ጋር የሚሠሯቸው የምርምር ስራዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ስለሚገኙበት ይህን ተሞክሮ የበለጠ ለማሳካት ተማሪዎቻችን በምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ የሚሳተፉበትን መንገድ በልዩ ሁኔታ በማዘጋጀት ለመተግበር እቅድ ይዘናል፡፡

ውድ ተመራቂ ተማሪዎቻችን

በምትሰማሩበት የህይወት ምዕራፍ ሁሉ ጥራት ያለው ሙያዊ አገልግሎት በመስጠት ዛሬ ያስመረቃችሁን ዩኒቨርሲቲ ስም በማስጠራት አምባሳደራችን እንድትሆኑ እያሳሰብኩ መልካም የህይወት ዘመን የምትጀምሩበት እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞቴን እገልጻለሁ፡፡

ተስፋዬ ሽፈራው (ዶ/ር)

የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት



Fikreselam Gared Mengistu (PhD)

Vice President for Information and Strategic Communication

## Congratulations on your achievement

Your graduation is a time of great celebration for you, your families and Bahir Dar University. It is a very memorable occasion for all of us and I wish you the very best on this important occasion. You have worked hard to achieve this milestone in your academic career and your hard work, dedication and discipline have paid off so that you are finally graduating.

Graduation is a time to recognize the completion of a program of study and to celebrate the commencing of a new chapter in your life. As the quest for scholastic success demands one to be energetic and driven to weigh the pros and cons of your decisions in life, I am certain that you will clearly demonstrate the outstanding qualities you met and surpassed in your academic career.

We continue to foster the relationship with you when you gravitate to the challenges generated by responsibility and set eagerness to make a difference in the world and leave your imprint on society. As you are engaged in such an intellectual journey, you are always welcome at our University.

Congratulations once again on successfully completing your program.

Fikreselam Gared Mengistu (PhD)

Vice President for Information and Strategic Communication



Nigus Gabbiye Habtu (PhD)
Scientific Director, Bahir Dar Institute of Technology (BiT)

## *Congratulations!*

I am quite certain that some four or five years ago when you enrolled as a freshman student into Bahir Dar Institute of Technology, one of the messages that was given to you was that the institute would like you to be a big ambassador of success for the institute. After your consistent hard work for over the last four or five years, you have come to the successful completion of your education, and hence to the attainment of your first degree.

Indeed, this moment marks the symbolic end to your individual and collective efforts made to achieve your goal. On this occasion, May I take this opportunity to ask you to reflect on whether the institute's thoughts were realized or not? Having said this, I am honored to have the opportunity to congratulate you for your hard work and dedication to your academic success. Thus, it is the right time to put forward my congratulations to all graduating students from **Bahir Dar Institute of Technology** (**BiT**) in particular and **Bahir Dar University** in general.

This is a special event for you and your families as you take this first step towards the beginning of new lives and environment. Your "maturity" both personally and professionally is one of our core values, which we believe enables you to benefit from a range of employment sectors. However, you should make use of the theoretical

ወደ ገጽ 6 ዞሯል



# መልዕክት

ከገጽ 5 የዞረ

knowledge and practical skills you acquired during your study and demonstrate your problem solving commitment to tackle the challenges of the community and make sure is up to the expected competence. The responsibility that you are expected to overtake requires tremendous commitment and dedication. Thus, I encourage you to stay focused and be genuine to yourself and also not to give up on your dreams no matter how difficult the challenge might be.

As the University embarks on its second generation after 50 years of journey, I hope you share my conceit in our effort for all that it has accomplished for its vision in moving forward, a vision having a national impact via dissemination of technologies centering to the need of the local community and industrial sector.

On the whole, on behalf of Bahir Dar Institute of Technology, I would like to thank the academic staff, administration staff, our partners and parents for accompanying our graduates on their educational journey, for you have brought our graduates to this point of time through many ups and downs. I would also like remind our graduates to be better prepared for this new, dynamic world, and remember to pay it forward as it is now your turn to teach minds, touch hearts, and transform lives. Remember, too, to move forward in the pursuit of our **Motto: Wisdom at the Source of Blue Nile.** Finally, I extend my sincere congratulations and best wishes for your future endeavor.

Nigus Gabbiye Habtu (PhD)
Scientific Director
Bahir Dar Institute of Technology (BiT), Bahir Dar University



Addisu Ferede Tesema (Asst. Professor)
Scientific Director,Ethiopian Institute of Textile and Fashion Technology (EiTEX)

As it is known, the Ethiopian Institute of Textile and Fashion Technology (EiTEX) is the pioneering institute offering higher education in the field of textile, garment and fashion design in Ethiopia since 1963. Since then, the institute has continued to grow with the introduction of B. Sc programs in Textile Engineering, Garment Engineering, Fashion Design, Textile and Apparel Merchandizing, Leather Engineering, Textile Engineering education and Garment Engineering Education. The institute also offers technical training and consultancy services to textile and garment industry and handloom sector. It is also focusing on giving impetus to research activities and technology transfer. Currently, the institute has 167 experienced academic staffs and the total enrollment includes about 3000 regular students trained in well equipped laboratories and workshops that acquired the state of art, equipment and machines.

The national responsibility of EiTEX is to produce skilled work force for the labor market and support the textile and garment industry through training consultancy and conducting applied researches.

Dear Graduates, we trained you keeping our national responsibility into consideration and believe that you are fit to the target. Now, your years of hard work and dedication to your academic success have paid off. On behalf of the members of the EiTEX), please accept my admiration and sincerest congratulations on your success. I know it is an exciting time for you and your families as it helped you gain intellectual enrichment towards the rest of your lives.
A driven personality and goal-oriented professionalism in your academic achievement is one of our core values, which make the dream in your profession better. Indeed, I appreciate and recognize your hard work. However, I also highly recommend you to stay focused in practicing the theories you studied and integrating them in your future professions, which determine the scope of your ultimate ambitions.

Taking everything into account, I have always been inspired by our graduates who take on the challenge of bettering themselves through education. This is a huge task that requires tremendous commitment and dedication. Thus, I encourage you to show a passion for your studies, demonstrate commitment to your future profession and also not to give up on your dreams no matter how difficult the challenge is. As you continue on your journey, know that you are always welcome.
Finally, I extend my warmest congratulations and best wishes for your future endeavor to all of you.

Addisu Ferede Tesema [Asst. Professor]
Scientific Director
Ethiopian Institute of Textile and Fashion Technology /EiTEX/, Bahir Dar University

እንኳን ደስ አላችሁ!



Mizanie Abate Tadesse (PhD)

Director, School of Law

## *Dear Graduates of 2015*

I am extremely excited to join with the entire academic and administrative staff of the School of Law to offer my pride and gratification on this achievement. Please accept my sincerest congratulations on the completion of your LL.B for Law Department students and BA education for students of Governance and Development Studies. The entire academic and administrative staff of the School is really proud of you. This is the culmination of years of hard work and study - a time to celebrate with your friends and family. I have no doubt that you will continue to serve as worthy ambassadors for the School by building upon our reputation for excellence. I also hope that you will continue your relationship with the School of Law.

During your stay in the School of Law, you have worked hard and persevered to become the best professional you wish to be. You have been given the tools you needed to pursue the dreams that brought you here, and; therefore, how you can choose to use those tools is now in your hands. I believe that all graduates of the School of Law, regardless of your chosen area of practice, have the opportunity to enrich the lives of those around you. As you embark upon and progress through your careers, I urge you to always remember why you chose your respective field and the sacrifices that you endured in order to make it happen: to serve our communities and improve the quality of life of its members with compassion, honesty and integrity.

I am confident that you will be able to effectively use not only the knowledge and the skills but also the values that you have gained during your time here in the School of Law.

I would also like to give special thanks to parents, spouses, children and friends of our graduates for their patience, understanding, sacrifices and support - both morally and financially during these challenging but rewarding years at the School. You can relish the shared feeling of pride in what your graduate has accomplished and the abundant opportunities ahead.

Best wishes for your future career.

Mizanie Abate Tadesse (PhD)

Director, School of Law



Essey Kebede Muluneh (PhD)
Dean, College of Science

On behalf of the College of Science, I extend my sincerest congratulations and best of luck to the graduates of 2015. I hope you had an enjoyable time in Bahir Dar University (BDU), and that our student centred and practice oriented teaching methodology has helped you gain much in your stay in the university. Now, you have graduated from the university. I understand that you have walked a long way to achieve this

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# መልዕክት

ከገጽ 6 የዞረ

milestone in your academic career.

Some of you might have succeeded in what you have planned; while others may not. Both success and failure are lessons for the life to come. Learn from what you have experienced, particularly your mistakes as it will uplift your confidence in tackling challenges.

The knowledge and skills you acquired are meant to change the quality of your life and serve our communities with compassion, honesty and integrity. I have no doubt that you will stay connected to BDU and continue to serve as our ambassadors.

I wish you the best in your future career.

Essey Kebede Muluneh (PhD)
Dean, College of Science,
Bahir Dar University



Embiale Beyene

Dean, Social Science Faculty

First of all, I would like to sincerely and warmly congratulate the graduates of 2015(2007 E.C). There is no doubt that it has taken much hard work to get to this point, and I admire you for it. I am pleased to congratulate your families and friends who have supported you throughout your time at Bahir Dar University with love and encouragement. Congratulations to your teachers who have shown so much devotion, knowledge, and skill in educating and coaching you. I also appreciate all of whom are celebrating with you today and who will cheer you on to your next steps which are coming fast.

Now, I would like directly urge the graduates about your leaving BDU and your journey ahead. When you leave BDU, most of you will go to a larger and more diverse environment that requires you to listen to , try to understand the ideas, perspectives and experiences of others. Your ability to listen to and learn from the perspectives and experiences of others will teach you a lot in the real work environment because it enlarges your own perspectives and experiences when you understand others, particularly those who are different from you. I hope you take the curiosity to learn from books, teachers, the environment around you and other people. If you have the curiosity and nurture it, you will never stop learning.

Dear graduates, so much emphasis has been placed to enable you demonstrate your outstanding qualities in your academic career, and many steps have been taken in our faculty to provide more comfortable conditions for your study. It is no secret that there is still much to do, but I assure you that we are determined and critical to offer better quality of education process for the present and the coming generation. Apart from this, I cannot ignore the fact that you take disciplines that reflect a certain strength of character, a commitment to keep working at it even when you are discouraged to get good at many things whether in the work environment or in pursuing postgraduate learning.

I am also grateful for the understanding and goodwill that you showed in supporting the faculty's management initiatives. Your roads are now diverging, and you will take your separate paths. I wish you the best of luck on the next stage of your journey which enables you to implement your goals and achieve your future success.

Embiale Beyene

Dean, Social Science Faculty



ዶ/ር በላይነህ አየለ አንተነህ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

የግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ ዲን

## ዉድ ተመራቂዎች

ከሁሉ አስቀድሜ ረጅሙን የትምህርት ጉዞ በማጠናቀቅ ለምረቃ በመብቃታችሁ ለእናንተና ከፍተኛ ሚና ለተጫወቱት ቤተሰቦቻችሁ በሙሉ በግብርናና አካባቢ ሣይንስ ኮሌጅ ስም እንኳን ደስ ያላችሁ እላለሁ:: ምንም እንኳ ትምህርት የማያልቅ የህይወት ምእራፍ ቢሆንም ዲግሪ ለማስገኘት ይበቃል ተብሎ የተወሰነዉን ስርአተ-ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ በማጠናቀቃችሁ በእጅጉ ደስ ሊላችሁ ይገባል:: ምክንያቱም እናንተ ከደረሳችሁበት ለመድረስ አስበዉ ያልተሳካላቸዉ ብርካቶች ናቸዉና.::

ይህን አጋጣሚ ተጠቅሜ ስለኮሌጃችን የተወሰነ መልዕክት ማስተላለፍ እወዳለሁ::

የግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ በ1998 ዓ.ም በስድስት መምህራን በአነዲት አነስተኛ ቢሮና በውስን ተማሪዎች ተመስርቶ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ከ120 በላይ መምህራን (ከ30% በላይ ዶክትሬት ዲግሪ ያላቸዉ)፣ ከ1500 በላይ ተማሪዎች፣ ራሱን የቻለ ግቢ ያለዉ መሆኑን ዛሬ ላይ ስንመለከት ኮሌጃችን ከዩኒቨርሲቲዉ እድገት ጋር አብሮ እያደገ ለመሆኑ ማሳያ ነዉ::

በአሁኑ ሰአት አስር የመጀመሪ ዲግሪ፣ አስራ ሶስት የማስተርስ ዲግሪ እንዲሁም ሁለት የዶክትሬት ዲግሪ ፕሮግራሞችን በማካሄድ ላይ የሚገኝ ሁሉን አቀፍ የግብርና ኮሌጅ በመሆን በእድገት ጎዳና በመገስገስ ላይ ይገኛል::

ኮሌጁ በግንባታ ላይ ሆኖ ትምህርት የጀመረ ሲሆን በአሁኑ ስአት 20 የተለያዩ ግብርና ነክ ቤተ- ሙከራዎች ግንባታ ተጠናቀዉ የቤተ- ሙከራ እቃዎችን በማስገባትና ስራ በማስጀመር ሂደት ላይ እንገኛለን:: ከእነዚህ በተጨማሪ ለተማሪዎች የተግባር ትምህርት መማሪያና መመራመሪያ የሚሆኑ የወተት ላም እርባታ፣ የዳልጋ ከብት ማድለብ፣ የበግ እርባታ፣ የአሳማ እርባታ፣ የንብ እርባታ እና አሳ ማባዣ ጣቢያዎች አቋቁሟል:: ቤተ- ሙከራዎች ሙሉ በሙሉ ስራ ሲጀምሩ ኮሌጃችንን በሀገሪቱ ካሉ ምርጥ የግብርና ኮሌጆች መካከል ቀዳሚ እንደሚሆን አልጠራጠርም::

ኮሌጃችን በአሁኑ ወቅት ሰላማዊ የመማር ማስተማር የስራ ሂደት ከማከናወኑ ባሻገር ከስድስት በላይ መጠነ ሰፊ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን ቀርፆ በማካሄድ ላይ ይገኛል:: ከእነዚህም ዉስጥ አይ ኤስ ኤስ ዲ፣ ፔሪ ፔሪ ዩ፣ ካስኬፕ፣ ዋሴ ጣናና የካካኒ ፕሮጀችቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ:: የአይ ኤስ ኤስ ፕሮጀክታችን በምርጥ ዘር አመራረት፣ ግብይትና አስተዳደር ዘርፍ ትርጉም ያለዉ ለዉጥ ያመጣ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ አርሶ አደርን ህይወት በመቀየር ላይ ያለ በመንግስት የዘር ዘርፍ ፖሊሲ ላይ አሻራዉን በማሳረፍ ላይ የሚገኝ የኮሌጁ ብሎም የዩኒቨርሲቲዉ ዋና መገለጫ ፕሮጀክት በመሆን ላይ ይገኛል::

ኮሌጃችን በምርምር ዘርፍ የሚያደርጋቸዉን እንቅስቃሴዎችም ለማሳይት ያክል በ2006 ዓ.ም የኮሌጃችን መምህራን ከ80 በላይ የጆርናል አርቲክሎችን በታወቁ አታሚዎች ለማሳተም የቻሉ ሲሆን ለዚህም ኮሌጃችን ብዙ የምርምር ዉጤቶችን በማሳተም ከዩኒቨርሲቲዉ አንደኛ በመዉጣት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ተሸልሟል›› በዚሀ አመትም ከ90 በላይ ህትመቶችን ለማሳተም አቅደን በመተግበር ላይ እንገኛለን:: ይህን ያክል በአጭሩ ስለኮሌጃችን ካልሁ በድጋሜ ተመራቂዎችን እንኳን ደስ አላችሁ በማለት መጪዉ የህይወት ጉዞአችሁ የተሳካ እንዲሆን ከልብ እየተመኘሁ መልእክቴን አጠናቅቃለሁ::

አመሰግናለሁ!!

ዶ/ር በላይነህ አየለ አንተነህ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

የግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ ዲን



ተማሪዎች በቤተ ሙከራ ውስጥ የተግባር ልምምድ እያደረጉ

Congratulations!



# መልዕክት



Seyoum Teshome (PhD)
Dean, Faculty of Humanities

***Congratulations! Dear graduates of 2015***

Dear graduates, you have spend a busy life since we first welcomed you to the Faculty of Humanities. You have been on different assignments, internships, practical attachments of various courses and written exams. In effect, you have gained a great deal of knowledge, develop different skills and learned "to think in scholarly way." Besides, you have established friendships that will last a lifetime and you now join an exceptionally talented and influential group – the graduates of Humanities Faculty.

Dear graduates, you would not be here today without the love and support of the people closest to you. Hence, I would like to express my appreciation to the instructors who have exerted much effort to make you successful and talented graduates. I would like to express my gratitude to your family, friends, roommates, classmates and all the university community for their contributions for your achievement.

The Faculty of Humanities is currently offering long term trainings in regular, summer, extension and distance programs. Degree program courses are being offered in all four departments in the faculty-English Language and Literature, Ethiopian Language(s) and Literature (Amharic), Journalism and Communications and Folklore (Cultural Studies). In addition, the Faculty runs Masters Degree in TeAm (Teaching Amharic), Linguistics, Literature, TEFL (Teaching English as a Foreign Language), Media and Communication; and PhD degree in TEFL (Teaching English as a Foreign Language) and TeAm (Teaching Amharic).

Our previous graduates have provided professional services in different governmental and non-governmental organizations all over the country.

Dear graduates, you have got the necessary knowledge and skills from your stay at our faculty that enable you to have a successful life in your future endeavor. I want to remember you that as a new graduate your strong ambitions in life will be achieved with hard work and diligent commitment.

The teaching and supporting staff of the faculty are proud of you because you have shown great accomplishment of your dreams.

Enjoy this momentous graduation day and, as you go out into the world, please keep us in your hearts as you will stay in ours.

Eventually, I would like to extend my sincere congratulations and best wishes for your future endeavor!

Seyoum Teshome (PhD)

Dean, Faculty of Humanities

እንኳን ደስ አላችሁ!

# እንግዳችን

ዶ/ር ፀሐይ ጀምበሩ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተምሮ ለቁም ነገር የበቃ እና በተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች ላይ በመስራት ውጤታማ የሆነ ምሁር ነው፡፡ ዶ/ር ፀሐይ ካካበታቸው ልምድ በመነሳት ስለሕይወቱ እንዲያጫውተን የናይል ጋዜጣ እንግዳችን አድርገነዋል፡፡ ቃለመጠይቁን እንሆ፣ መልካም ንባብ!!



**ጥበበ ዓባይ፡-** ዶ/ር ፀሐይ ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆንክ ከልብ እናመሰግናለን፡፡ ቃለመጠይቃችንን እንዲህ እንጀምር፡፡ እስኪ ስለ ትውልድህ፣ ልጅነትህና ትምህርትህ አውጋን፡፡

**ዶ/ር ፀሐይ፡-** (በመጀመሪያ በተባእት የገለጽሁት ሁሉ እህቶቼንና ልጆቼንም እንደሚመለከት እወቁልኝ፡፡ የቅድሚያም ሆነ የግብዝነት ጠኔ ይዞኝ ሳይሆን ለአሁን ቦታ ስለሚቆጥብልኝ ብቻ ነው፡፡)

የተወለድኩት በ1948 ዓ/ም ደብረ ማርቆስ ከተማ ነበር፡፡ ለእናቴ የስእለት ልጅ ስሆን ለወላጆቼ የመጀመሪያውም ነበርሁ፡፡ ድህነት እና መሃይምነት በሰፊው በገነነበት ከተማ፣ ከተማረ አባት እና ጠግቦ ከሚያድር ቤተ ሰብ ነበር የተገኘሁ፡፡ አባቴ በታሪክ፣ በህግ፣ በሃይማኖት እና በአደባባይ ስርአቶች በቂ እውቀት የነበራቸው እውነተኛና ሀገር አፍቃሪ ሰው የነበሩ ሲሆን፣ እናቴ ደግሞ እንደ ሁሉም የጊዜው እናቶች ሁሉ ሕይወቸውን ለልጆቻቸው መስዋእት የሰጡ ሴት ነበሩ፡፡ የልጅነት ሕይወቴ ፍጹም ደስታ የሞላው ነበር፡፡ ህጻናትን ጥሩ ምግባር ለማስጨበጥ ዱላና ስድብ ዋና ማስተማሪያ ሆኖ በብዛት በሚሠራበት ማሕበረ ሰብ ውስጥ፣ እኔ ገደብ የሌለው ፍቅር፣ አድናቆትና አክብሮት ወላጆቼ እየመገቡኝ በማደጌ ከጥቂት እድለኛ ህጻናት መሀከል አንዱ ሆንኩ፡፡ አሁን ዘመናዊው ሳይኮሎጂ የሚሰብከው የህጻናት አስተዳደግ፣ በባህላችንም የነበረ ለመሆኑ አሁን ስገነዘበው በጣም እኮራለሁ (እውቀቱ እና ጥበቡ በጥቂቶች ብቻ ተይዞ መቅረቱ ቢያሳዝነኝም)፡፡

አባቴ የእድገት ዘመኔን እየተከተሉ የሀገሬን ታሪክ፣ ሃይማኖቴን፣ በራስ መተማመንን፣ ትህትናን፣ እውነተኝነትን እና በርካታ የሕይወት ክህሎቶችን አስርጸውብኛል፡፡ ለአቅመ ትምህርት ስደርስም በባህላዊው ት/ቤት ዳዊት ደግሜ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ት/ቤት እስከ 8ኛ ክፍል ተምሬአለሁ፡፡

ጎጃም ጠቅላይ ግዛት የነበሩት ት/ቤቶቸ በጣም ጥቂት ነበሩ - በወረዳ አንድ ካለ እንኳ ብርቅ ነበር፡፡ ት/ቤቶቹ መቀመጫቸው ድንጋይ ሻል ሲልም ግንድ፣ ክፍሎቹ የጭቃ፣ ወለሎች አፈር የነበሩና በእበት ተለቅልቀውም ወዲያው አቧራው የሚጨስባቸውና የሞያሌ ቁንጮች እንደ ልብ የሚፈነጩባቸው ነበሩ - በብዙዎቹ፡፡ ደግነቱ የህጻናቱ መኖርያም ከዚህ የባሰ ስለነበረ ቅሬታ ተነስቶም አያውቅም፡፡ የማርቆሱ ት/ቤታችን ግን በአሁን ዘመን ከሚገኙት ምርጥ ት/ቤቶች ቢወዳደር እንኳ የማይተናነስ ነበር፡፡ ግድግዳዎች በጥበበኛ ገንቢዎች የታነጹት የድንጋይ ክፍሎች፣ በመዶሻ ቢመቷቸው እንኳ የማይፈርሱት የሲሚንቶ ወለሎች፣ በቂ ብርሃን የሚያስገቡት የመስታወት መስኮቶች፣ ጠንካራና ምቹ ዴስኮች ደረጃቸውን መጠበቃቸው ብቻ ሳይሆን፣ ለትምህርት ግብአቶች ከሞላ ጎደል የተሟሉ ነበሩ - የእጅ ሙያ፣ የስእል፣ የግብርና፣ የስፖርት ወርክ ሾፖች እና ስቱዲዮዎች ሁሉ እስከ ቤተ መጻህፍትና የሳይንስ ላቦራቶሪዎች ሁሉ የተሟሉለት ነበረ፡፡ ከዚያ ት/ቤት በመማሬ በጣም እድለኛ ነበርኩ፡፡ (2ኛ ደረጃው ወደ ሌላ ግቢ ሲሄድ መጻህፍቱ ለሁለት ተከፍለው ከፍ ያሉት አብረው ሄደው ነበር፡፡ ከህጻናት እና ወጣቶች መጻህፍት በሁሉም (genere) እስከ ክላሲካል እና ዘመናዊ የትምህርት፣ የስነ ጽሁፍ እና ፍልስፍና መጻህፍት ነበሩ፡፡ ሁሉም ዩኤስ ኤይድ አርማ አላቸው - ያው በእርዳታ የተለገሱ፡፡ ከላይበራሪው ተርፈው 3 ሙሉ የስቶር ክፍሎች ውስጥ ተከምረው ነበር፡፡ ተክለ ሃይማኖትም እንዲሁ፡፡ በ1978 ዓ/ም የደርግ ሶሻሊዝም "በሰረጸበት" ወቅት እኔም እዚያው መምህር ነበርኩና መመስከር እችላለሁ፡፡ 'መጻህፍቱ ቦታ አጣበቡ' ተባለ፤ ቀጥሎ 'የኢምፔሪሊስት መጻህፍት ስለሆኑ አድሃሪ ጸረ-ህዝብ አስተሳሰብ ስለሚያራምዱ ይቃጠሉ ተብሎ ተወሰነባቸው'፡፡ በሁለቱም ት/ቤቶች በርካታ መጻህፍት እሳት በላቸው፡፡ ከዚያ "ብልሃት" ተገኜ፡፡ ለሚፈልጉ በጨረታ ተሸጠው የውስጥ ገቢ ያዳብሩ ተባለ፡፡ በኪ.ግ 10 ሳንቲም ሂሳብ ተቸበቸቡ፡፡ አምስትና ስድስት ጭነት መኪናዎች ሲጫኑ አይቻለሁ፡፡ ሙሉ ሙሉ ሥራዎች - እነ ሼክስፒር፣ እነ ቶልስቶይ፣ ዲክንስ፣ .. እነ ኒውተን፣ ራስል፣ ሆመር .. ከእሳት የተረፉት በሳንቲም ተለውጠው ሄዱ፣ የት እንደገቡ አይታወቅም፡፡ ዳይሬክተሩን ከየርእሱ አንድ አንድ መርጬ እንድናስቀር እያለቀስኩ ለመንኩት፣ በናፋቂ 5ኛ ረድፈኛነቴ አፌዘብኝ - ብዙ መለኪያ ዊስኪዎች እንደወጣቸውም አውቃለሁ፡፡ አሁን

ወደ ገጽ 9 ዞሯል



# እንግዳችን ...

ከገጽ 8 የዞረ

ግን ይመስገነው! እድሜ ለጉግል! የፈለገ አሁን ሊያገኛቸው ይችላል::)

የጊዜው ዋና የትምህርት ማሳለጫ ዘዴም እንደ ንጉሥ የሚከበረው መምህር የሚያዝዘውን መፈጸም ነበር:: ተማሪው ባዶ እቃ ስለሆነ መምህር እውቀት ይደፋበታል - ተማሪ አምጣ ሲባል ሳያጎድል፣ ሳይሸርፍ መመለስ ነው:: ህጻኑ እንደ ጎልማሳ ስለሚቆጠርም ባህርዩ የበሰለ እንዲሆን ይጠበቃል:: ጥያቄ ለመመለስ ለተቸገረ ወይም ከስርአት ዝንፍ ላለ ተማሪ ደግሞ መድሃኒቱ አለንጋ ነው፣ ዱላ ነው፣ ጥፊ ነው፣ መንበርከክ ነው:: የሚገርመኝ በዚያ ሁሉ ቅጣት መሃከል ህጻኑ ሁሉ "ያጠፋል"፣ ይወቃል - የፒሪዬዱ ግማሽ በጩኸትና በዱላ ያልቃል - ደግነቱ የምንማረው ቀኑን ሙሉ ስለነበረ ትምህርቱ አልቀረብንም:: አንድ ዋና ጉዳይ ግን ልመስክር - ይህ ሁሉ የመምህራን "ጭካኔ" በጊዜው በነበረው አስተሳሰብ ለበጎ ተብሎ ነው፤ ሁሉም መምህራን ህጻናቱ በሚገባ እንዲያውቁና ጎበዝ ሆነው ሕይወታቸው እንዲቀናላቸው በሙሉ ፍላጎትና በንጹህ ልብ ይደክሙልን ነበር::

እኔ ከዚህ ሁሉ ቅጥቀጣ መሃከል እንደ እንቅርጣጥ ባቂላ የተረፍሁ ነኝ:: አንዴም አጥፍቼ አልተገረፍኩም፣ የመንፈስ ጥቃትና የውርደት ቃል ከአንድም መምህር አልደረሰብኝም (አልፎ አልፎ መላው ክፍል ሲቀጣ ከመቅመሴ በስተቀር!):: እንዲያውም በተቃራኒው መምህሮቼ እያደነቁኝ፣ እያስጨበጨቡልኝ 8ቱን ዓመታት በደስታ ዘልቄአለሁ:: እንጃ! የህጻንነት የወላጆቼ አያያዝ የረዳኝ ይመስለኛል - ቀጥተኛና የሆነውን ነገር ሳላዛባ እናገር ስለነበረ፣ የሆነ ጥፋት ተሠርቶ መምህራን እውነቱ ሲቸግራቸው እኔን እያስነሱ እንድመሰክር ያደርጉኝ ነበር:: ባልወድደውም እውነቱን ከመናገር ወደ ኋላ ብዬም አላውቅም (ጥሩ ነገር ሲያዩ መምህራን ለሁሉም ልጆች አድናቆትና ሙገሳ ሁሌም ይሰጣሉ):: ታዲያ በዚህ አድናቆትና ሙገሳ መሃከል ያደግሁ ልጅ "ጎበዝ" ብሆን የሚገርም አይደለም:: እዚህም በጣም የታደልሁ ልጅ ነበርሁ ማለት ነው::

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴንም በዚህ ዓይነት መንገድ አጠናቅቄ ልዑል በእደ ማርያም ት/ቤት ገባሁ:: በጊዜው የነበረው የትምህርት ስርዓት ጥቂት ልሂቃንን ለማፍራት የታለመ ስለሚመስል፣ ብዙሃንን አግላይ ስለሆነ የሚተች ቢሆንም፣ የ2ኛ ደረጃን የትምህርት ጥራት ከማስጠበቂያ ፈርጆች አንዱ የበቁ መምህራንን ማፍራት ስለሆነ፣ የበእደ ማርያም ት/ቤት ለዚህ ተግባር ተመደበ:: በየጠቅላይ ግዛቶቹ ካሉት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች እጅግ ጎበዝ ተማሪዎችን ከ11ኛ ክፍል ቀልቦና ጠልፎ በመውሰድ ዩኒቨርሲቲ አሰልጥኖ በመምህርነት ማሰማራት:: የ12ኛን መልቀቂያ ለማለፍ ማንም እርግጠኛ ስለማይሆን፣ የድሃ ልጆች ዋነኛ ዒላማዎች ነበሩ:: ይህ አሠራር ያልጠረጠሩ የድሃ ልጆችን ፍርሃት በመጠቀም (exploit) ስለነበረ መልካም ባይሆንም፣ የበቁና ጥራት ያላቸውን መምህራንን ለማፍራት የተሰጠውን ቅድሚያ ሳስበው ግን እደነቃለሁ:: መንግሥታችን የትምህርት ጥራትን ለማዳበር አሁን እያደረገ ያለውን ርብርብና የሚመድበውን በጀት ሳይ በጣም ብረካም፣ ከመሰናዶ ት/ቤቶች መጥተው አነስተኛ ውጤት ስላላቸው፣ ሌሎች ኮሌጆች ስላልተቀበሏቸው ወደ መምህር አምራች ፋኩሊቲዎች የሚመደቡትን ስገምት ግን ይከፋኛል:: በእርግጥ በሶሻሊስቶች አሠራር ተማሪዎችን ያለፍላጎታቸው በግድ መመደቡ የግለሰቦችን መብት ስለሚጥስ መንግሥታችን ተቸግሮ እንደሆነ ይገባኛል፤ ሆኖም መፍትሄ ያለው ይመስለኛል:: መምህርነትን በገበያ ተወዳዳሪ የሙያ መስክ ማድረግ ይቻላል:: (በአእምሮዬ የተወሰኑ የመፍትሄ ሃሳቦች ይመላለሳሉ፣ የሚጠይቀኝ ባገኝ ልተነፍሳቸው ዝግጁ ነኝ::)

የኮሌጅ ትምህርቴን ያጠናቀቅሁ እዚሁ ፔዳ ሲሆን ከአስተማሪዎቼ፣ ከሠራተኞችና ከጋደኞቼ ጋር የፍቅር፣ የደስታ፣ የአድናቆትና የሰፊ የእውቀት ሽመታ ዘመናትን አሳልፌአለሁ:: እዚህም ከፍተኛ ባለ እድለኛነት ይሰማኛል::

በነገራችን ላይ በደርግ የድብደባ ካምፕ ውስጥ እኔም እንደ በርካቶቹ ወጣቶች ገብቼ ነበር:: ያ ሁሉ ወጣት በዱላ እየተቀጠቀጠ፣ በስለት እየተተለተለ፣ በእሳት እየተለበለበ ሲሰቃይና ለአካል ጉዳትና ለሞት ሲዳረግ፣ ገራፊዎች እንደለመድኩት ፍቅርና አድናቆት ባይሰጡኝም፣ አንድም ጥፊ እንኳ ሳያርፍብኝ በጣም ቀላል ስድቦችን ብቻ ተንፍሰውብኝ ለቅቀውኛል:: ይህ ያለመደብደብና የመንፈስ ጥቃት ያለመቀበል እድል እንዴት ተሰጠኝ እያልኩ ሁሌ እደነቃለሁ - የፈጠረኝንም አመሰግናለሁ::

**ጥበበ ዓባይ:-** ፔዳ ከተመረቅህ በኋላ እዚህ ተመልሰህ እስክትመደብ ድረስ የት የት ሠራህ?

**ዶ/ር ፀሐይ:-** መጀመሪያ እዚህ ከነበረው መ.ማ.ተ፣ ቀጥሎ ደ/ማ ሁለተኛ ደረጃ በመጨረሻም ጎንደር መ.ማ.ተ በመምህርነት አገልግያለሁ:: የመማር ዓለምና የሥራ ዓለም እጅግ የተራራቁ ናቸው:: አገሬ ደሃ ነበረችና ዋና ቀጣሪም መንግሥት ነበርና የሥራ እና የእድገት እድሎች አስቸጋሪ ነበሩ:: የመወዳደሪያው ሕግ በወረቀት የተጻፈና የተደነገገ ቢሆንም፣ በተግባር ግን በርካታ ጠመዝማዛዎች ሞልተውታል:: ቅጣት፣ ዱላ፣ ማዋረድ ዋነኛ የማስተዳደሪያ መሣሪያዎች ሆነው በወላጆችም፣ በመምህራንም በመንግሥትም ላይ በሠለጠኑበት ከባቢ ያደገ ህብረተሰብ፤ ራሱን በምንም ዘዴ የሚከላከል፣ ተጠራጣሪ፣ ተንኮለኛና ክፋተኛ፣ ካልተገቡ ንክኪዎች ውስጥ ለመቀላቀል የማይመለስ ብዙ ሰው ቢኖር አይደንቅም:: ስለዚህ የቅጥርና የእድገት ሁኔታ በየጊዜው በሚለዋወጡ የቅጥፈት ዘዴዎች ስለሚሞላ ተገቢ የሆኑ እጩዎች የሚሸነፉባቸው ክስተቶች ይበረክታሉ:: እኔም ምንም ልምድ በተንኮሉና በሽፍጡ ሜዳ ስላልነበረኝ፣ ያሰረጽሁት ቀጥ ያለው እውነት በትምህርቴ ላይ ቢሠራም በዚህ የሥራ ሕይወት ጨዋታ ላይ ስላልሠራ፣ የዚህ ሜዳ ሰለባው ነበርሁ:: ግፍ ሊባሉ የሚችሉ ሸፍጠኛ በደሎች እዚህ ፔዳ ከተቀጠርሁ በኋላ፣ ማርቆስም፣ ጎንደርም ተፈጽመውብኛል:: እድገትም፣ የውጭ የትምህርት እድልም ቀርተውብኛል:: ሰው ነኝና አዝኛለሁ:: በትክክለኛው የጨዋታ ሕግ እንዳልተበለጥሁ ስለማውቅና ችግሩ የመነጨው በከባቢው ጨካኝ የአስተዳደግ ሁኔታ መሆኑን ስለምገነዘብ፣ እነዚያ ግፈኞችና የክፋት ሰዎች ራሳቸው የሚታዘንላቸው ናቸው እያልሁ ተጽናንቻለሁ:: በመጨረሻም ጊዜው ሲደርስ አአዩ ገብቼ 2ኛ ዲግሪዬን ወስጄ ተመልሼ ባዳዩ መምህር ሆኜ መጣሁ::

**ጥበበ ዓባይ:-** እስቲ ስለ ትዳርህና ቤተሰብህ አጫውተን::

**ዶ/ር ፀሐይ:-** ትዳር መስርቼ ልጆችን ወልጄ መኖር ከጀመርሁ ሩብ ምዕተ ዓመት አለፈኝ:: ሦስት ልጆችን አፍርቼአለሁ:: ከወላጆቼ ያገኘሁትንና በሳይኮሎጂ ያወቅሁትን የልጆች አስተዳደግ ተሞክሮ እየተገበርሁ ራሳቸውን፣ ወላጆቻቸውን እና አገራቸውን ጠቃሚና አኩሪ ልጆችን ለማፍራት እየጣርሁ ነው:: ገደብ የሌለውን አባታዊ ፍቅርን እየሰጠሁ ስርአትን፣ የማይረካን የእውቀት ፍለጋን እና የአገር ፍቅር እንዲድርባቸው እየጣርኩ ነው:: እስካሁንም መልካም መንገድ ላይ በመሆኔ በጣም እድለኛ ሰው ነኝ እላለሁ::

በሌላ በኩል ከባለቤቴ ጋር ስለ ትዳር ያሉን እሴቶች እጅግ የተለያዩ እንዲያውም የተቃረኑ ስለሆኑ፣ በሁሉም የሕይወት ፈርጆች አንስማማም:: ይህም ለዘወትር ጭቅጭቅ፣ ኩርፊያ፣ ለንዝንዝና ለጠብ ስለዳረገን ሀዘንተኛ ሕይወት እንድገፋ አድርጎኛል:: ጸጸትና ብስጭት በርካታ ጊዜዬን በልተውታል:: ለምን እንደማንለያይ ወዳጆቼ ጠይቀውኛል:: ይህ ለእኔም ሆነ ለባለቤቴ መልካም እንደሆነ አውቃለሁ፤ ሆኖም ልጆች ለስነ ልቦና ችግር ይጋለጣሉ የሚለው ፍርሀት ያመዝንብኛል:: በሳይኮሎጂ approach-avoidance conflict ይባላል:: በበርካታ የሕይወት ጉዞዎቼ እድለኛ ብሆንም በትዳርስ ፍጹም እድለኛ አይደለሁም::

አባቶቻችን ወጣቶችን ለትዳር ሲያጣምሩ የተጋቢዎችን የቤተሰብ ሁኔታ ይመረምሩ ነበር:: አሁን የዘመኑ ሰዎችና የብዙሀን መገናኛው ሁሉ የሁለቱ ተጋቢዎች መፋቀር ብቻ ይበቃል እያሉ ብዙ ለፍልፈው ደንዝዘናል:: እኔም የዚህ ጩኸት ሰለባ ነበርሁና ለሀዘን ተዳረግሁ:: የተጋቢዎች ካውንስሊንግ የሚባል መስክ አለ፤ እኔም በራሴ ተምሬው አሁን እያስተማርሁት ነው:: የትዳር ባህርይ፣ በተለይም ቅራኔ አፈታት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚወርድ (generational) ለመሆኑ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

Congratulations!



# እንግዳችን ...

ከገጽ 9 የዞረ

ተረጋግጧል፡፡ ኋላ ቀር የተባሉት አባቶቻችን በጣም ሊቆች ስለነበሩ ቀድመው አውቀውታል - አሁን ለእኔ እጅግ ዘግይቷል፡፡ ለወጣት ተመራቂዎች ግን ከዚህ ከእኔ መከራ ሞራል ሊወስዱ ይገባል፡፡ የምታፈቅሩትን/ዋትን ወጣት ቤተሰቦችን ባህርያትና እሴቶችን መርምራችሁ ከእናንተ ባህርያትና እሴቶች ጋር መጣጣሙን አረጋግጡ፡፡ ለጋብቻ ውሳኔአችሁን ከዚህ በኋላ አድርጉት፡፡

**ጥበበ ዓባይ፡-** ባዳዩ ከተመለስክ በኋላ 3ኛ ዲግሪህንም ሠርተሃል፣ በተለዩ አመራር ቦታዎችም አገልግለሀል፡፡ ምን ተግባራትን ፈጸምክ፣ ምን ፈተናዎችስ ገጠሙኝ ትላለህ?

**ዶ/ር ፀሐይ፡-** ከባድ ጥያቄ ስለሆነ መዘብዘብ አለብኝ፡፡ ሦስት ቃላትን (እስከ ዘራቸው) ሳስባቸውም ሆነ ሳዳምጣቸው እንደ መላዕክት ዜማ ያከንፉኛል፣ እንደ ማር ወለላ ይጣፍጡኛል - ኢትጵያ፣ ድንግል/ልጇ እና ፔዳ/ባዳዩ፡፡ ሦስቱም የማንነቴ (identity) መግለጫዎች ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ እናቴ ናት፣ ዝቅ ብዬ ጀምሬ ወደ ላይ ብሄድ - ወላጅ እናቴ፣ ወላጆቼ፣ ቀዬዬ፣ ወንዜ፣ ክልሌ፣ አገሬ፡፡ አሁን ዘመን አገር ይቀድማል - የለም ብሔር ይቀድማል እያሉ ሲከራከሩ የሰማሁ መሰለኝ፡፡ ይሄ የእንቁላልና የዶሮ መቀዳደም ችግር ይመስለኛል፡፡ እንደሁኔታው (context) በእኩልነትና በአንድነት ሁሉም የሚገልጹኝ ይመስለኛል፡፡ ሳይቀዳደሙ አንድ ላይ መሥራት አይችሉምን? እያልሁም አስባለሁ (ዘባረቅሁ እንዴ!)፡፡ ሁለተኛው ቃል ግልጥ ስለሆነ ልለፈው፡፡

የፔዳን ልንገርሽ፤በ1971 ባ/ዳር ፖሊስ ጣቢያ ለ31 ቀናት ታስሬ ነበር፡፡ ያኔ "ትልቅ ማርክ" ያመጣ ተብዬ ስሜ በየሰሌዳው ተለጥፎ ስለነበር ሁሉም አድናቆት እየሰጠኝ ነበር፡፡ በድንገት በፖሊስ ተይዤ ስሄድ ብዙ ሠራተኞች አዘኑልኝ፡፡ የሚደንቀኝና የሚያስደስተኝ ግን ፔዳ የመንግሥት ተቋም ሆኖ ስርዓቱን ለማፍረስ የተሳተፈ ወጣት ከጉያው ተደብቆ ሲገኝ፣ ይህንን አውግዞ ርምጃም መውሰድ ሲችል፣ ያደረገው ግን በግልባጩ ነበር፡፡ የነበሩት መኪናዎች ጥቂት ስለነበሩ ለሥራ አልበቃ ብለው ችግር ነበረ፡፡ አስተዳደሩ አንዷን መኪና መደበልኝ፡፡ በቀን ሦስት ጊዜ ምግብ ታመላልስልኝ ጀመር፡፡ እናት የካፌ ሠራተኞች በእለቱ ካለው ምግብ ምርጡን ከሽነውና ይበልጥ አጥመው፣ በርከት አድርገው ይልኩልኛል፡፡ የእኔ ምግብ በርካቶች እስረኞችን ሲመግብና ሲደነቅልኝ ከረመ፡፡ ለአንድ ጊዜ እንኳን ሾፌር ዘይግቶብኝም፣ ተሰላችቶብኝም አያውቅም፡፡ በኋላም ወደ ማርቆስ ስወሰድ ብዙ የፔዳ ባልደረቦች እንዳዘኑልኝ ሰምቻለሁ፡፡ ተፈትቼ ስመለስም የመልሶ ቅበላ ማመልከቻ ጊዜ ስላልነበረ፣ አካዳሚክ ኮሚሽኑ ሕጉን ጥሶ፣ ምንም ሳልጉላላ፣ ጠብቀ ሳልባል ትምህርቴን ቀጥያለሁ፡፡ በጊዜው የነበራችሁት - ሁላችሁንም እወድዳችኋለሁ፡፡

ታዲያ ለፔዳ/ባዳዩ የተለየ ፍቅር ቢያድርብኝ ምኑ ይገርማል? በዚህ የአምልኮ በሚመስል ፍቅር ውስጥ ነበረ ባዳዩ ውስጥ የማስተማርም የአመራርንም እድሎችን ያገኘሁት፡፡ በ1994 የፕሮግራም ኃላፊ ሆኜ መሥራት ጀመርሁ፡፡ ቀስ እያለ ግን ችግሮች ተከመሩና ዩኒቨሪሲቲው ቀውስ ውስጥ ገባ፡፡ አመራሩን መለወጥ ስላስፈለገም የታሰቡት እጩዎች ሁሉ እዚህ ጣጣ ውስጥ መግባቱን ፈሩና የሹመት ጥያቄውን አንቀበልም አሉ፡፡ እኔ የመጨረሻው አማራጭ ነበርሁ፡፡ አቅም የለኝም በማለት እምቢኝ ልል ብሞክርም፣ 'ታዲያ ሁሉም አሻፈረን ሲል ምን ትላለህ?' ስባል ተቀበልኩት፡፡

ቀጥ ያለውን ተራራ መውጣቱን ተያያዝሁት፡፡ ጎን ለጎን የማኔጅሜንት ትምህርቴን ወጥሬ አጠናሁ፡፡ በርካታ ችግሮች በአጣሪ ኮሚቴ ተመዝግበው ስለነበረ፣ እኔ ዋና ዋናዎችን እየመረጥሁ በስርዓት (ለይስሙላ፣ ግር ግር ሳይሆን) እያጠናሁ የፈታኋቸው ይመስለኛል፡፡ የተለመደው የአመራር ዘዬ በጣም ባህላዊ ስለነበረ (በመላው አገሬ)፣ በአለቃና በምንዝር ያለው የኃይል ርቀት (power distance) በጣም ሰፊ፣ አለቃ ሁሉንም አዋቂ፣ የበታች የታዘዘውን ብቻ መፈጸም የሚገባው፣ ወዘተ... ነበረ፡፡ እኔ ይህንን የአመራር ዘዬ በጭንቅላቱ ገለበጥሁት፡፡ መሪ ተባባሪና ጓደኛ እንጂ እርሱም እንደ ሁሉም ሠራተኛ ድክመት ያለው፣ መማርና መሻሻል የሚገባው፣ ሠራተኞችም ሊያስተምሩትና ሊቃወሙት የሚችሉ፣ ለጋራ ዓላማ ፍቅር እና ሃቅ እንደሚጠቅሙ፣ ሁሉም በስብእናው ሊከበርና እውቅና ሊሰጠው እንዲሁም የጥቅሙ ተካፋይም መሆን እንዳለበት ... በተግባር ለማሳየት ሞክሬአለሁ፡፡ ይሳካልኝ አይሳካልኝ አልወቀው እንጂ፣ የትራንፎርሜሽናል መሪ ባህርያትን ለማንጸባረቅ ጥሬአለሁ፡፡ የተለያዩ የአመራር ዘዬዎችን - ለቀቅ ወደሚሉት (እንደ በመራመድ መምራት ዓይነት) ለመጠቀም ለፍቻለሁ፡፡ በየሥራ ክፍሉ እየዞርኩ ተምሬአለሁ፡፡ በየቢሮው እየወረድሁ መፈረም ያለበትን እዚያው ስፈርም፣ መጀመሪያ ተላላኪዎች ተደናግጠው ነበር፣ በኋላ ግን እንደወደዱልኝ አውቃለሁ፡፡ "ክብር"ን የሚወድዱ መምህራን ዩኒቨሪሲቲውን አዋረደ በማለት ወቅሰውኛል፡፡

የንባብ ክህሎት ለሁሉም ተግባር እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ እኔ በፍጥነት የማንበብ ስልጠናን አባቴም መምህሮቼም ሰጥተውኛል፡፡ እኔም በራሴ አዳብሬው ፈጣን ሆኛለሁ፡፡ በተለይም ፔዳ ስማር ለሦስት ዓመታት በላይብራሪው በትርፍ ሰዓት ስለሠራሁ፣ እግረ መንገዴን በርካታ ስነ-ጽሁፎችን ለማንበብ በመብቃቴ ክህሎቴ እጅግ ዳብሮልኝ ነበረ፡፡ ይህ ለፕሬዚደንት ተግባሬ ጠቀመኝ - የአቤቱታና የመመሪያ ጋጋታ ሲከመርብኝ በፍጥነት እያነብኩና እየወሰንሁ መጉላላት ቀነሰ፤ እንዲያውም ቢሮዬ ባዶ እየሆነ በroutine ተግባራት መጠመዴ ቀረልኝ፡፡ የሥራ ባልደረቦቼ መፈጸም የሚገባቸውን ሳያደርጉ ሳገኝ ደርቤ ብዙ ከውኛለሁ - በርካታ ሌሊቶችን ደክሜአለሁ፡፡

ዋና መሣሪያዎቼ (ቢያንስ በልቤ) እውነት፣ ፍቅር፣ ትህትናና የተማሪዎች፣ የመምህራንና የሠራተኞች ደስታ ነበር፡፡ ለተራ ተወዳጅነት ሳይሆን ፍጥረቴ ነው፡፡ የመንግሥት መመሪያዎች የሚያሠሩ ናቸው፡፡ ችግሩ ያለው የቢሮ ኃላፊዎች ጠማማ አተረጓጎሞችና በመሀከል የተለያዩ ስነ ምግባራዊ ያልሆኑ ማነሳሻዎች ስለሚጋረጡባቸው ነው፡፡ ሕጉን ሳልጥስ የአሠራር ሰንሰለቱን እየቆራረጥሁ ለመሥራት ጥሬአለሁ፡፡ ለሰባት ዓመታት በከፍተኛ አመራር ደረጃዎች ሳገለግል፣ አርኪ የምላቸው ውጤቶችን ያስገኘሁ ይመስለኛል፡፡

- ከነበረው ቀውስ ወጥተናል፣ በየስብሰባው የምወድደው ባዳዩ ሲሳቀበት ሳይ እበሳጭ ነበር - ከታላላቆቹ ተከባሪዎች ዩኒቨሪሲቲዎች እኩል ሲከበር አይቻለሁ፡፡
- አዳዲስ ፋኩሊቲዎችና ት/ክፍሎች በግል ጥረቴ ተከፍተው አሁን አውራ ሆነዋል፡፡
- የውስጥ ገቢ አድጎ ከእዳ ወደ ባለሀብትነት ባዳዩ ተሸጋግሮልኛል፡፡ መምህራንና ሠራተኞችም ከጥቅሙ ተካፋይ ነበሩ፡፡
- የአሠራር መመሪያዎች፣ ደምቦች፣ ስርዓቶች በጥናት እየተመሰረትሁ አስጸድቄ የተወሰኑት አሁንም ይሠራባቸዋል፡፡
- ቀሪው ታሪክ ነው፡፡

አንድ ልጨምርሽ፤ - በ1996 ም/ፕሬዝዳንት ስሾም 3 ሴት መምህራን ብቻ ነበሩ፡፡ ስለሴቶች ብዙ ተሰብኳል፣ በርካታ "ፈንድ" ለየጥናቱና ለየሴሚናሩ ወጥቷል፡፡ ለውጥ ግን የለም፡፡ በየፈርጁ ስለ feminist approaches ጥቂት አንብቤአለሁ፡፡ ወንዶች በቀረጹት የሕግ ዓለም ሴቶችን ማሳተፍ አስቸጋሪ መሆኑን ስለማውቅ የነበረውን የመቅጠሪያ መስፈርት ለጊዜው ሰረዝሁት (ሥልጣን ለመልካም ነገርም በጣም ጠቃሚ ነው)፡፡ በየት/ክፍሎቹ የሴት መምህራን መበራከት ከአዎንታዊነቱ ባሻገር ለሴት ተማሪዎች ሞዴልና ጠበቃ እንደሚሆኑም አውቃለሁ፡፡ በሁለት ዓመታት ውስጥ ወደ 200 የሚሆኑ ሴት መምህራንን ቀጠርኩ፡፡ የተነሳብኝ ጫጫታና ተቃውሞ መቼም አይረሳኝም - ሁሉ ግብ ግብ ገጠመኝ (ዓለማየሁ ከጎኔ ነበር)፡፡ ኃይሉ ነበረኝና፣ ችግር ቢፈጠር ደግሞ ተጠያቂውም እኔው ነበርሁና ቀስ እያለ አቧራው ጠራ፡፡ ውጤቱን አጥንቼዋለሁ - ሴት መምህሮቻችን የጠሩ መምህራት ሆነው ዘልቀዋል፡፡ እስከ አሁን የሚደንቀኝ ግን - በዚህ ጉዳይ ለመነጋገር ከት/ሚኒስቴር የሴቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ ወደ ቢሮዬ መጣች፡፡ ስለ ገድሌ አድናቆት ትለግሰኛለች ብዬ ጓጉቼ ነበረ፡፡ ነገር ግን ሕግ በመጣሴ፣ የትምህርቱን ጥራት ለመጉዳት ዝቅተኛ ጂፒኤ ያላቸውን ሴቶች በመቅጠሬ .. እረ ስንቱ ... የሂስና የትችት ናዳ አወረደችብኝ፡፡ ደጋፊዬ ብዬ የገመትኳት ኃላፊ አናንቃኝ ስትሄድ ግን መገረም እንጂ ሀዘን አልተሰማኝም፡፡

መልካም ጥረትን ከማድነቅና ከማበረታታት ይልቅ ማጣጣል የሚቀናቸው ሰዎች አሉ፡፡ ለምን እንደሆነ አይገባኝም - ሳይኮሎጂስቶች እንደ ፈርጃቸው ቢለያዩም፣ የህጻንነት በደል የሰዎችን እይታ ስለሚያጣምመው፣ በሁሉም insecure ስለሚሆኑ እና ተከላካይነት ወዘተ.. ስለሚቃኙ ነው ይላሉ፡፡ ወይስ መጠናት ያለበት ሌላ የሐበሻ ሳይኮሎጂ ይኖር? - እኔ አቅሙ ያለው ቢሞክረው ልናቃናው እንችላለን እያልሁ አስባለሁ፡፡

እኔ በጎ የዋልኩላቸው፣ በደላቸውን ያካካስኩላቸው፣ የተነፈጉትን የአካዳሚ እድገት ወይም የትምህርት እድል ያስገኘሁላቸው በርካታ መምህራን አሉ፡፡ ጥቂቶቹ ከሥልጣን ስሻር ጠሉኝ፣ ሰላምታ ነፈጉኝ፣ እንዲውያም የተወሰኑት ሊያጠቁኝም ሞከሩ፡፡ ለእነዚህ ሰዎች ምክንያት ብፈልግ ብፈልግ አላገኘሁላቸውም፡፡ አዝኜላቸው፣ ይቅር ብያቸው፣ ሁሉንም ረስቼ ወደ ፊት እየቀጠልኩ እገኛለሁ፡፡ የተወሰኑትማ ራሴን ሳልጠቅም መሻሬ ከንቱነቴን እንደሚያሳይ በቀጥታም በጎሜም ጎሽመውኛል፡፡ ከመሳቅ በስተቀር ምን ለማለት ይቻላል? እነዚህ ሰዎች ከሚገኙበት ያልበሰለ instrumental የሞራል ደረጃ ራቅ ወዳለው ድህረ የተለመደው (ኮህልበርግ) ወደ ተጠጋው የሞራል ደረጃ የምገኝ ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን የምወደወደው ፔዳና እጅግ የበዛው ሠራተኛና መምህር እስካሁን ድረስ ፍቅሩንና ክብሩን እየሰጠኝ በደስታ አለሁ፡፡

**ጥበበ ዓባይ፡-** መልካም፤ እስቲ በጥናትና በፕሮጀክት ተግባራት ያደረግሀቸው ሥራዎች ካሉህ ብትነግረን፡፡

**ዶ/ር ፀሐይ፡-** ውጤታማ ጥናቶችን ለማካሄድ ፍላጎቱ ነበረኝ፡፡ አቅሙም (እውነተኛውን ለመሥራት) መነሻውም የለኝም መሰለኝ፡፡ እውነቱን

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

እንኳን ደስ አላችሁ!





# እንግዳችን ...

ከገጽ 10 የዞረ

ልተንፍስልሽ፤ እኔ በማውቀው በትምህርት መስክ የሚሠሩ ጥናቶች በአብዛኛው ቅጥፈት ያለባቸው ናቸው፡፡ ማንም ደፍሮ ተናግሮም አሳይቶም አያውቅም - እህ! ችግሩ በየአጥቁ እያለ ማን እውነታ በትክክል የሚጠቁም (reality) ምርምር ሊሠራ ይችላል? በርካታዎች በየጆርናሎቹ ያነበብኳቸው መሠረታዊና የትግበራ ጥናቶች የዳሰሳ ዓይነቶች ሲሆኑ መረጃው የሚሰበሰበው ሌሎችን በመጠየቅ ነው፡፡ መላሾቹ የጥናት ባህሉም ስለሌላቸው፣ ጥቅሙም ደርሷቸው ስለማያውቅ፣ ለይሉኝታ ሲሉ ይመልሳሉ፡፡ ግድ የለሽ የሆነ የሃሰት መረጃ ይሰጣሉ፡፡ አጥኚዎች ካገኟት "ፈንድ" ምናልባትም አብዛኛውን ለማትረፍም ጭምር የመላሾችን ጊዜና ጉልበት በነጻ ስለሚጠቀሙ፣ የተሰጣቸው መረጃ ከሚጠበቀው የምዕራብ ውጤቶች ጋር የት የለሌ ይርቅባቸዋል፡፡ መፍትሄው ጥናቱን መተውና በሌላ ዘዴ መሞከር ነበር፡፡ ግን እድገት፣ ማእረግ፣ ኩራት ላይገኙ ስለሆነ የገፉበት ይመስለኛል፡፡ ዳታውን ከሊትሬቸር ጋር እንዲመሳሰል ማስተካከል፣ "መጥበስ" ይጀመርና በዚሁ አልቆ ተጠና ይባላል፡፡ የባሰም አለ - ውስጡን ለ .. እንጂ - የጥናት ሥራ እየሠራ መሆኑን እንኳን ሳናውቅ በጆርናል ሲታተም ያስተዋልኳቸውም አሉ፤ ጥናት መደበኛና የአደባባይ መስሎኝ! (የሚሊታሪ፣ የህዋ፣ የኮርፖሬሽን ወይም የሀገር ሚስጥራዊ ምርምር ካልሆነ)! እንዲህም ይታማል - ሌላ አገር የተሠሩ ያልታተሙ የተማሪ ወረቀቶችን ሰብስቦ ማምጣት፣ እንደ ሁኔታው እየመዘዙ የከተማውንና የት/ቤቱን ስም ኢትዮጵያዊ አድርጎ ጥቂት ቀያይሮ ለህትመት መላክ፡፡ በዚህ ላይ ወገን ከታከለበት ቶሎ ይታተምና እንደ ብዛቱ ሹመቱ ይከተላል፡፡ ይህ ለክብር፣ ለኩራት፣ ለሥልጣንም ጠቃሚ ነው፡፡ የምርምር ዓላማ ክፍተትን በሳይንሳዊ ዘዴ ለመሙላት የሚደረግ ፕሮፌሽናላዊ የውስጥ ቃጠሎ ካልሆነና ራስን በተገኘው መንገድ ለማግነን ከሆነ - ይህ ቅጥፈት የሚወገድ አይመስለኝም፡፡

እስቲ እንፈትሽ፤ የትኛው ጥናት ነው በሃገራችን ሁኔታ በትክክል ተሠርቶ፣ ሌላው ሰው ደግሞ ፈትሾት ለትክክለኛነቱ ተመስክሮለት የሆነ ቲዮሪ፣ ሞዴል፣ የሂሳብ ቀመር ወዘተ... ተገኝቶለት ለተግባርም ሆነ ለተጨማሪ ን/ሃሳብ መነሻ የሆነ? ምንን እናያለን? እውነት የጎደላቸው ምርምሮች ደግሞ ለውጥም አያመጡም፣ እውቀትም አይጨምሩም፡፡

አንተስ ልባል ነው፡፡ አንድ ጊዜ አ.አ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ሳስተምር ስለ የውልደት ተራ እና የትምህርት ውጤት ዝምድና ላጠና ለሁለት ክፍል ተማሪዎች ስማቸውንና ለወላጆቻቸው ስንተኛ ልጆች እንደሆኑ መጠይቅ አዘጋጅቼ በተንሁላቸው፡፡ የሰጡኝ ምላሽ እስካሁን ይገርመኛል - አብዘኛዎቹ ከ50ኛ እስከ 130ኛ ልጅ ነን ብለው መለሱልኝ - በዚያው ጥናቱ ቀረ፡፡ በኋላ የ2ኛና 3ኛ ዲግሪዎች መመረቂያ ጥናቶችን ግድ መሥራት ነበረብኝ፡፡ ሁለቱም ምዕራብ የተሠራባቸው ስታንዳርድ ስኬሎች ቢሆኑም ለሁሉም ባህል የሚሆኑ ነበሩ፡፡ ምላሾች ግን ባብዛኛው የጤነኛ አልነበሩም፡፡ ሁለት ምርጫዎች ነበሩኝ - ጥናቶችን ማቆምና መውደቅ ወይም ዳታ ጠብሶ መመረቅ፡፡ በመውደቅ የሚደርስብኝን ውርደትና ቤተሰቤም በችጋር መጠበሱ የሚታሰብ አልሆነልኝም፡፡ ስለዚህ ዳታዎችን ጠባባሼ፣ አስተካክዬና እንዲመስል አድርጌ "ጎበዝ" እየተባልኩ ተመርቄአለሁ፡፡ በቅጥፈት ሥራዎቼ ችሎታየን ባስመሰክርም፣ እውነት ስላልሆኑ ጥቅም የላቸውም፡፡ አሁን ተናዘዝሁት - እፎይ! እነዚህ ሁለት ዲግሪዎችህ አይገቡህም ብሎ ሊገፍፈኝ ለሚመጣ ሰው በደስታና በክብር አስረክበዋለሁ፡፡ ይህ ሰው ግን ቅጥፈት ያላቸውን ጥናቶች ያልሠራ ሊሆን ይገባዋል፡፡

በብዙ አገሮች እንደሚደረገው፣ የታተሙ ጥናቶችን ሌሎች በመድገም (replicate) እንዲሠሩዋቸው ዩኒቨሪሲቲዎች ቢያበረታቱ፣ ገንዘብም ቢመድቡ ችግሩ የሚቀንስ ይመስለኛል፡፡ ዋናው ግን፣ ባሕሉ እንዲሰርጽ የተለያዩና ቀጣይ ተግባራት የሚጠይቅ ይመስለኛል፡፡ ደግሞም ጥናቶች ምክንያትና ውጤትን የሚፈትሹ እንዲሆኑ፣ ለእነዚህ የገንዘብ ድጋፉን ማዞርም የሚያስፈልግ ይመስለኛል፡፡ በቡድን እንዲሠሩ ማበረታታትም መልካም ነው - መቼም በጋራ መስረቅ ቢቻልም ከባድ ይሆናል፡፡

እኔ እንግዲህ ስሙ ቢቀርብኝም ከ30 በላይ ያልረቡ (የማይታተሙ) ጥናቶችን ሠርቼ፣ ጥቅሞችንም አስገኝቻለሁ

- የገበያ ጥናቶችን አካሂጄ፣ በውጤቶችም ፕሮጅክቶች ቀርጨ፣ ሥራዎቹም ተተግብረው ባዳዩና ተገልጋዮቹ በጣም ተጠቅመዋል፡፡
- የፍላጎት ጥናቶች እያካሄድኩ ፋኩሊቲዎችም፣ ት/ክፍሎችም ተከፍተዋል፡፡
- የማኔጅሜንት ጥናቶችን እየሠራሁ መመሪያዎች ተቀርጸዋል፣ ችግሮችን ለመፍታት ሞክሬአለሁ፡፡
- ባለፉት አምስት ዓመታት ደግሞ ለአንድ በጎ አድራጊ ድርጅት በአንደኛ ደረጃ ህጻናት ንባብ ዙሪያ ወደ 5 ጥናቶችን ሠርቻለሁ - በውጤቶችም የአብክመ ት/ቢሮ ከፍተኛ ዘመቻ አከናውኖ የህጻናትን ንባብ ክህሎቶች በእጅጉ አሻሽሎታል፡፡

በተጨማሪም ዳታ እየጠበስኩ ልቦለድ ጥናት ከማቀርብ፣ በቁርጡ ልቦለድ ድርሰት ብጽፍ ይሻለናል ብዬ አንድ ሁለት ጀምሬ እልፈሰፈሳለሁ፡፡ የስንፍና ጠበል ባገኝ፣ ያንን ተጠምቄ ልጨርሳቸው እመኛለሁ፡፡

**ጥበበ ዓባይ፡-** የምረቃ ወቅት ስለሆነ አንተ ትዝ የሚልህ ምረቃ ካለ ብታወጋን፣ እንዲሁም ለተመራቂዎች መልእክት ካለህ ብታስተላልፍልን፤

**ዶ/ር ፀሐይ፡-** በ1975 ዓ/ም ስመረቅ የሜዳሊያ ተሸላሚም ስለነበርሁ ያኔ የተጨበጨበልኝን አልረሳውም፡፡ በዚያች ውብ የፔዳ አዳራሽ አስመራቂ እና ተመራቂዎች ተጠቅጥቀን ሞልተን፣ ዲኑ የተለመደውን ከተናገሩ በኋላ ስሜን ሲጠሩ እስካሁን ድረስ አይቼውም ሰምቼውም በማላውቀው ድምቀት፣ ሁሉም ከመቀመጫው ተነስቶ ለበርካታ ደቂቃዎች ከልቡ አጨብጭቦልኛል፡፡ በወሬ የሰማሁት ለስታሊን ተደረገለት የሚባለው ጭብጨባ ቢበልጠው እንጂ (ስቀልድ ነው) እጅግ ደማቅ ነበር፡፡ ያኔ ፔዳ ለሰጠኝ ፍቅር አሁንም አመሰግናለሁ፡፡

የዘንድሮ ተመራቂዎችን እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ፡፡ ይህን አሁን የገለጽሁላችሁን ሸጋ የሆነ የምረቃ ባሕል እንድታስቀጥሉት አደራ እላችኋለሁ፡፡ የምትመረቁት ራሳችሁ ብቻ ሳትሆኑ ጓደኞቻችሁ ጭምር ስለሆኑ፣ የእናንተ ተራ ደርሶ ብትመረቁም ስርዓቱ እስኪጠናቀቅ አድምቃችሁ መጨረሳችሁ ጨዋነት ነው፡፡ ሁሉም እየመከራችሁ ስለሆነ አላሰለቻችሁም፡፡ ሆኖም ሀገራችሁ የሰጠቻችሁን ብድር እስከወለዱ በቅንነት በማገልገል መልሱላት፤ ዳያስፖራ አትሁኑ አትመኙትም - ሆድን ሞልቶ በውርደት ከመኖር፣ ለሀገር ሠርቶ ሆድን መሙላት እንደሚሻል አትርሱ እላለሁ (ከበደ ሚካኤል በተረትና ምሳሌ ፩ኛ መጽሐፍ ስለ ሶቅራጥስ አንድ ተርከው ያስተማሩት "በባዕድ አገር ሀብታም ሆኖ ከመኖር ይልቅ በተወለዱበት አገር ተቸግሮ መኖር ...ገጽ ፷፱" ፡፡

**ጥበበ ዓባይ፡-** ባዳዩ በ2017 አፍሪካ ከሚገኙት 10 ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ እሆናለሁ ብሎ ራዕይ አስቀምጧል፡፡ ራዕዩን ለማሳካት ምን መደረግ አለበት ትላለህ? አመራሩ፣ መምህራንና ሠራተኞች የሚጠበቅባቸው ምን ምን እንደሆነ ብትገልጽልን፤

**ዶ/ር ፀሐይ፡-** ባዳዩ በ2017 እደርስበታለሁ ብሎ ያስቀመጠው ራዕይ ይማርከኛል፡፡ ባለፉት 10 ዓመታት በጣም ሩቅ ተጉዟናል - በ30 ዓመታት ሌሎች የማይደርሱበትን መንገድ፡፡ የቀረን መንገድ ጨርቅ ነው፡፡ የ40፡40፡20 ምጣኔም እንደሚሳካ አውቃለሁ፡፡ ምክር ለመስጠት ግን እኔ ማን ነኝና? ይሁን ካልሽ ግን ሁላችንም በየራሳችን የሚመላለስ ሃሳብ ስለሚኖረን፣ ጠቀመም እርባናም አይኑረው ጥቂት ልሠንዝር፡-

ሀ) አመራር፡ - ብዙዎቻችን አመራር ላይ የምንመደበው በአጋጣሚ ነው፡፡ መሪ መሆን መልካም አጋጣሚም ሸክምም ነው፡፡ እኔ የስኳርና የግፊት ህመሞችን ሸምቼበታለሁ፡፡ ዩኒቨሪሲቲ ከፍተኛ የሆነ staff professionalization ያለበት ተቋም ነው - በመሪዎችና በመምህራን መሃከል የችሎታ ልዩነት የለም፡፡ ስለዚህ የአመራር ጥበቡን ለመማር ዝግጁ መሆን፣ ከራሳቸው ከየሚመለከታቸው (ከጥበቃው ጀምሮ) እውቀቱን መቅሰም ያስፈልጋል፡፡ እንዲህ ሲደረግ ሁሉም አስተዋጽዖ እንዳለው፣ እውቅና እንደተሰጠው ስለሚረዳ ተነሳሽነቱ ይጨምራል - በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ማለት ይሄ ነው፡፡ በቅንነትና በእውነት ለማገልገል፣ የራስንም ስም ትቶ ለማለፍ ከተጣረ፣ ተከታይ ማፍራት ቀላል ነው፡፡ ደግሞም አንድ መሪ ለሁሉም የበታች ሊጥም አይችልምና፤ የተቋም ፖለቲካ አይቀሬ ስለሆነ፣ የሚገጥምን ፈተና ቂም ባለመያዝ፣ በትዕግስት፣ በመመካከርና ይቅር በማለት ማለፍ ይቻላል፡፡

ለ) መምህር - አሁን የሚገኘው ወጣት መምህር እድለኛ ነው - በገቢም በሰፊ የትምህርት እድልም፡፡ በሁሉም የሕይወትና የሥራ ፈርጆች ወደ ላይ የመመንጠቅ ፍላጎት መቆም ባይኖርነትም፣ መምህራን አሁን ባላቸው የተመቸ ሁኔታ መደሰትንና መርካትንም መማር ይገባቸዋል፡፡ ከባዳዩ 2017 ራዕይ ለመድረስ መምህራን ከምሁር ደረጃ መድረስ ይጠበቅብናል፡፡ የ3ኛ ወይም 2ኛ ዲግሪዎችን መያዝ ምሁር አያደርጉም፡፡ መቼም አሁን ባዳዩ ውስጥ ምሁራን ይገኛሉ ብሎ የሚከራከር ካለ፣ ለቃሉ የሰጠው ብያኔ ቀለል ያለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአሁኑ ሳዓት ሁላችንም የሠለጠንን (trained) ነን፡፡ ምሁርነት በተሰማሩበት መስክ ፍጹም መመሰጥና የን/ሃሳቦችንና የተግባር ክፍተቶችን ለመሙላት፣ የሠፈሩን እውቀት ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጆችም እውቀት ጥቂት ማበርከትን ይጠይቃል፡፡ ከሙያ ባሻገር በተለያዩ የማህበራዊ፣ ከባቢያዊ፣ ሀገራዊ ... ጉዳዮች ላይ ማጥናት፣ መሳተፍና ተሰሚነትን መግዛት ያሻል፡፡ ምሁርነት እውነተኛነትን፣ ለሌሎች ሞዴል መሆንን፣ ትህትናን፣ አነስተኞችን ማገዝን ... ይፈልጋል፡፡ ምርምር ለማካሄድ ስንነሳ ዋና ዓላማችን ለዝና፣ ለክብር፣ ለማእረግ ከሆነ ቅጥፈትና ማምታታት በራሳቸው ጊዜ ጥናቱ ውስጥ ሰተት ብለው ይገባሉ፡፡ የለም፣ ለምርምርና ለአገልግሎት ስንነሳ ክፍተቱን ለመሙላት ይሁን፣ አንዱ ባይሳካ ሌላ ምርምር መጀመር ነው - ኤዲሰን ስንት ጊዜ ነው ምርምሮቹ የከሸፉበት? እውነተኛ ውጤት እያስገኘን ስንሄድ ወደ ምሁርነት ጉዞ ገባን ማለት ነው - ከተደፈረ መንገዱ አጭር መሆኑን ከምሁራን ታሪክ ማየት ይቻላል፡፡ ጥቅሞቹ፣ ክብሩና ታዋቂነቱ ተደርቦ (ባንፈልገው እንኳ) ይመጣል (bi product) ይለናል ፍራንክል፡፡

ዩኒቨሪሲቲዎችና የጥናት ማዕከላት ግሩም የሆነ የሙያ መዋቅር (career structure) አላቸው፡፡ ሌሎች መ/ቤቶች እና የከፍተኛ ት/ተቋማት አስተዳደሮች የፒራሚድ ቅርጽ አላቸው፡፡ ከታች ያለው ሠራተኛ ወደ ላይ እንዲያድግ፣

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

Congratulations!



# እንግዳችን …

ከገጽ 11 የዞረ

ከላዩ የነበረው ሰው ወይ ወደ ላይ መውጣት አልያም መወገድ አለበት (መ/ቤቱ ካልተስፋፋ በስተቀር)፡፡ ስለዚህ፣ ሽኩቻና መጠላለፍ ቢከሰት አይገርምም፡፡ የመምህራን ግን ጣሳ ቅርጽ ነው ያለው፡፡ ሁሉም አቅሙ እስከ ፈቀደለት ድረስ ወደ ላይ መተኮስ ይችላል፡፡ ለሽኩቻና ለፍትጊያ ቦታ የላቸውም፡፡ እንዲያውም ትብብርና መረዳዳት አብሮ ለመሰቀል በጣም ይጠቅማሉ፡፡ ምሁር ደረጃ ለመድረስም ቀላሉ መንገድ ይህ ነው፡፡ አንዱን የምእራብ ዩኒቨሪሲቲ ውሰዱና የመምህራኑን ፕሮፋይል መርምሩ - መልካም ተሞክሮዎች ትቀስማላችሁ፡፡

አንዳንዴ እዚህ የማስተውለው ግን፣ ግር ይለኛል፤ የዶክትሬት ዲግሪውን ባመጣ በነጋታው፣ የአካዳሚክ እድገቱ በጸደቀለት በሳምንቱ ከየበላዬ (ት/ክፍል፣ ኮሌጅ፣ ኃላፊ … ወዘተ) በምን አንሳለሁ (እኔ እበልጣለሁ) ብሎ በመኮፈስ አለቃን በበነነ በተነነው ግብ ግብ መግጠም ጤነኛ አካሄድ አይደለም፡፡ አለቃው ደካማ ቢሆን እንኳ፣ ተገቢውን ክብር ሰጥቶ ለማሻሻል መጣር ይቻላል፡፡ ግብ ግቡ ግን ወደ ጠብና ቂም ስለሚያመራ፣ በየት/ክፍሉ በቡድን እየሆኑ ሲጎነታተሉ፣ አንዱ የቋጠረውን ሌላው ሲፈታ፣ አንዱ የገነባውን ሌላው ሲንድ፣ በየስብሰባው እንደመመካከር ስህተትን እያጎሉ ሲካሰሱና ሲወጋገዙ መኖር ይመጣል፡፡ ታዲያ በዚህ ሁኔታ የባዳዩ ራዕይስ ይቅር፣ እንዴት ራስንስ ወደ ምሁርነት ማሸጋገር ይቻላል? ወደ 2000 የሚሆኑ መምህራን አሉ፤ የአመራር ቦታዎች ግን ሃምሳና ስድሳ ቢሆኑ ነው፡፡ እንዴት ነው በርካቶች የሚቋምጡላቸው? እኔ እንዲህ እላለሁ፡ - አንድ መምህር ለቦታው ተስማሚ ቢሆን እንኳ፣ ተለምኖ እንጂ ታግሎና ተሻፍጦ ለአመራር ቦታ ራሱን እጩ ማድረግ አይገባውም - ሌላ አማራጭ ሞልቶታልና! (አንድ በብዙ መከራ ለፍቼ የትምህርት እድል እንዲያገኝ የረዳሁት መምህር አለ፡፡ በእድሜ በጣም ስለምበልጠው "ጋሼ" እያለ ነበር የሚጠራኝ፡፡ ዶክተር ሆኖ ከመጣ በኋላ ፀሐይ (ሲያሰኘው ደግሞ ዶ/ር) እያለ ይጠራኝ ጀመረ፡፡ ዲግሪው እንዲህ የሚያስኮፍስ ከሆነ ዓላማውን ስቷል እላለሁ፡፡)

ይልቅስ ራዕይ 2017ን ከልብ ሰንቆ ምን ልናበረክት እንደምንችልና ከባዳዩ ጋር አብረን እንዴት እንደምናድግ እያሰብን ከልብ ብንለፋ፣ በቀላሉ ደርሰን ሁላችንም እንረካለን እላለሁ፡፡

ሠራተኞች፡ - የባዳዩ ሠራተኞች የትም የማይገኙ እጅግ ተወዳጅና ተባባሪ ናቸው - በሚገባ አውቃቸዋለሁ፡፡ ልናቀርባቸው፣ ልናከብራቸው፣ ከጥቅሙም ከትምህርት ዕድሉም ልናሳትፋቸው ግን ይገባል፡፡ ራዕዩን ወደ ግቦችና ወደ ዓላማዎች ስንሰባብረው፣ ልናሳትፋቸውና ድርሻቸውን እንዲያውቁ መርዳትም ያስፈልጋል፡፡ ጠንክረው እንደሚሠሩም አውቃለሁ - የመምህራንን ያክል በርካታ የሥራ አማራጮች ስለሌላቸው፣ ከልብ እንደሚለፉና ወደ ራዕዩ በፊት መሪነት እንደሚፈጥኑ አምናለሁ፡፡

እህ! ተራራውን ወጥተን ሜዳው ላይ ስለማንቆም በእርግጠኝነት ምርጥ ዩኒቨሪሲቲ እንሆናለን፡፡

ላጠቃልልሽ መሰለኝ፤ ስለ ራሴ መልካም መልካሙን ብቻ መናገሬ ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ እንዳይመስልሽ፡፡ መጥፎ፣ ግምና ደካማ ባህርያትና ምግባራት ሞልተው ተርፈውኛል - ብዙ ቁና ስፍር! አብዛኛዎችንም አውቃቸዋለሁ፡፡ ብዘረዝራቸው ምን ይፈይዳሉ ብዬ ነው እንጂ፡፡ እንዲያው ሳስበው ዶስቶይቪስኪ የጻፈው The Idiot የሚባል መጽሀፍ አለ፡፡ የያኔዋ ሩስያ እና የአሁኗ አገሬ ይመሳሰሉብኛል፡፡ ዋና ባህሪው - ሙይሽኪን ይባላል - ጅል ነገር፡፡ የዚህን ሰው ባህርያት የመሰሉ በርካታ መሳለቂያዎችና ጅላጅል ምግባራት ሞልተውኛል - ግን እወዳቸዋለሁ፡፡ በቅጥፈት እየተሳካልኝ ከምኖር ጅል ሆኖ መኖር ይሻለኛል፡፡

በመጨረሻ ሆን ብዬ የጎዳሁት ሰው የለኝም፡፡ ሳላውቅ የጎዳኋችሁ ይቅር በሉኝ፡፡ በተለያየ ምክንያት የጠላችሁኝ፣ የጎዳችሁኝ፣ ግፍም የሞከራችሁኝ፣ ባልሠራሁት ያሳቀላችሁብኝ ወንድሞቼና እህቶቼ ሁሉ፣ እኔ እወድዳችኋለሁ፣ እናንተንም ይቅር ብያችኋለሁ ይቅር እንድትሉኝ ከልቤ እለምናችኋለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!!

ጥበበ ዓባይ፡- ዶ/ር ፀሐይ ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን!!

**እንኳን ደስ አላችሁ!**

# ያልተጠበቀ አጨራረስ (የገጠመኝ ጽሑፍ)

በሜሮን ጌታቸው

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሁፍ ት/ክፍል እጩ ምሩቅ

ሠኞ በአስረኛው ወር 2007 ዓ.ም እንደዚህ ሆነ፡፡ ትላንት የታቀደው ዕቅድ ግቡን መታ፡፡ ከትላንት ልጀምር፡፡ ትላንት የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ባህል ማዕከል የቲያትር ቡድን የመሰብሰቢያ ቀን ነበር፡፡ በስብሰባው ዕለት ዜድ አልመጣም፡፡ ዜድ ማለት ከትምህርት ውጪ በባህር ዳር ከተማ በተለያዩ ክበባት ውስጥ ቲያትር የሚሰራ የተለያዩ የቲያትር ስልጠናዎችን የወሰደ እና የተውጣጣ ዕውቀቱን ሳይሰስት ለቲያትር ቡድን አባላት የሚያካፍለን የቲያትር ክፍሉ መሪ ነው፡፡ ታዲያ ዜድ ዛሬ የቀረው ሲመስለኝ ሲመስለኝ ሀሙስ የምርምር ስራውን የሚያቀርብበት ቀን ስለሆነ ቴንሽን ይዞት ነው፡፡ ሌሎቻችን የቲያትር ቡድኑ አባላት ተሰባስበት የዜድን የ3 ዓመታት ቆይታ መጠናቀቅ አስመልክተን በተለይም ዕውቀቱን ሳይሰስት ስለሰጠን ለምስጋና የሚሆን ስጦታ ለመስጠትና በማዕከሉ የመሰነባበቻ መርሃ ግብር ስለምንሰራው ቲያትር ለመወያየት ነበር፡፡ በውይይቱ ላይ ሁለት ሀሳብ ተነሳ አንዱ ሀሳብ ለዜድ የሚሰጠው ስጦታ ተማሪነታችንን ያማከለ ይሁን የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለምን 'የቁጩ አንሰራውም' (fake) የሚል ነበር፡፡

ሁለተኛውን ሀሳብ ያመጣው የምድር ጉድ ነገሮችን አቀነባብሮ ሰነዘራቸው፡፡ ሀሳቡ እንዲህ ነበር፡፡ ዜድ በተፈጥሮው በጣም ኩሩ፣ ሴትን ልጅ ከስራ ውጪ የማይቀርብ፣ ፍቅረኛ የሌለው እና ሴትን ማቅረብ የማይወድ ነው፡፡ ስለዚህ ለሱ በምናዘጋጀው ልዩ መርሃ ግብር ላይ አንዲት ሴት የፍቅር ታሪክ አለኝ በማለት ታቅርብና ያፈቀረችው ሰው እዚህ ይገኛል በማለት ዜድን ወደ መድረክ በመጋበዝ ፍቅሯን ትግለፅለት የሚል ነበር፡፡ ይህንን ሀሳብ ተናግሮ እንደጨረሰ አብዛኛው የቲያትር ቡድን አባላት ሀሳቡን ወደዱት፡፡ ጨዋታን የማይወድ ማን አለ? ሀሳቡ ይሳካ ዘንድ በማዕከሉ ውስጥ ያለነው 15 ሴቶች እኔንም ጨምሮ ለውድድር ታጨን፡፡ ውድድሩ ጥሩ የፍቅር ትወና የምትችል ሴትን ለመምረጥ ነበር፡፡ ዕድሌ አሊያም እጣ ጦሴ ሆኖ ውድድሩን አሸነፍኩ፡፡

ከውጤቱ በኋላ መመሪያዎች ተሰጡኝ፡፡ ከመመሪያዎቹ መካከል አንድኛው ዜድ በጣም ኩሩ ስለሆነ "እንቢ አልፈልግም" ቢልም ማልቀስና መማጸን ግዴታ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በአቋሙ ጸንቶ አልበገርም ካለ ራስን ስቶ መድረክ ላይ መውደቅ ነው፡፡ ከዚያም ሌሎች መጥተው አፋፍሰው እንደሚያነሱኝ የሚገልፅ ነበር፡፡ ገጥሜአለሁ! ገጥሜአለሁና ወደፊት! ሁሉንም ሀሳብ አሜን ብዬ ተቀበልኩ፡፡ የዜድ የሞባይል ቁጥር ተሰጠኝ፡፡

በተባልኩት መሰረት አመሻሽ ላይ ደወልኩለት፡፡ እውነትም ኮስታራና ቁጡ ነው፡፡ በድምጹ ያስታውቃል፣ያስበረግጋል፡፡ ከሱ ይልቅ ጓደኛው ስልኩን ተቀብሎ በተንሾካሾከ ድምጽ ሳይብረሪ መሆናቸውን ነግሮ ስልኩን ዘጋው፤ ምንም አላልኩም፡፡ በቃ ልጁ ኩሩ ነው የነገው ስራ አይሰራም ብዬ ተስፋ አልቆረጥኩም፡፡ መልሶ ይደውላል በማለት ጠበኩት፡፡ በርግጥም ደወለ ብዙ አወራን፡፡ በመልዕክትም ሀሳብ ተለዋወጥን፡፡ በቀጣዩ ቀን የትዕይንቱ ሰዓት ደረሰ፡፡

ወደ መድረክ ተጋብዤ ንግግሬን ጀመርኩ፡፡ በሽኙቱ ምሽት የባህል ማዕከል አባላትና ተመራቂ ተማሪዎች ታድመው አዳራሹ ጥቅጥቅ ብሏል፡፡ እኔም በለመድኩት የትወና ጥበብ ዓይን ያወጣ የውሸት ታሪኬን ዘክዝኬ ተናገርኩ፡፡ ወደ መድረክ ዜድ ተጋብዞ መጣ፡፡ መልሱ ምን ይሆን? የብዙዎቹ ጥያቄ ነበር፡፡ እውነታውን የማያውቁት እሱና አንዳንድ እንግዳ ታዳሚዎች ብቻ ናቸው፡፡ የተጠበቀው ሌላ የሆነው ሌላ ሆኖ አረፈው፡፡

እንደተገመተው ያልሆነ ያልተጠበቀው ነገር ተከሰተ፡፡ ዜድ ጉድ አፈላ፡፡ "እኔም እኮ እወድሻለሁ" የሚል መልስ ሰጠ፡፡ ግራ ተጋባሁ፣ ከአሁን አሁን እንቢ ብሎኝ ትወናዬን እጀምራለሁ ያልኩት ልጅ ትዕይንቱ ተገታብኝ፡፡ ማድረግ የምችለው በማዕከሉ ስም የተገዛለትን ስጦታ መስጠት ብቻ ነበር፡፡ በስጦታው ከልቡ ተደሰተ፡፡ ዜድ ከመድረኩ ሲወርድ የቀረበው ትዕይንት "የቁጩ"(ውሸት) እንደሆነ ነገሩት፡፡ በጣም ከመናደዱ የተነሳ መድረኩ ላይ ወጥቶ ብዙ ቃላትን ወረወረ፡፡ "በማይሆን ቀልድ የሰው ሕይወት ለምን ታበላሻለችሁ?" ብሎ ጠየቀ፡፡ መልስ የለም፡፡ ሀሳቡን ያመነጩት እንኳ አስገምጋሚ ቁጣውን ሰምተው መልስ ሊሰጡ ቀርቶ ቀና ብለው ማየት አቃታቸው፡፡ ወዲያው ለጨዋታ የተባለው ነገር መስመሩን እንደሳተ እና የሰው ስሜት እንደነካ ስረዳ ጸጸት በህሊናዮ ተሰራጨ፡፡

እንደምንም የታቀደው ዝግጅት ተጠናቀቀ፡፡ ከመርሃ ግብሩ በኋላ በግል አግኝቶኝ ተነጋገርን፡፡ "እውነት ነው ወይስ አንቺም እንደእነሱ ስታናግሪኝ የነበረው፣ በሜሴጅ ስትልኪልኝ የነበረው የፍቅር ታሪክ ሁሉ የውሸት ነው?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ምን የተለየ መልስ ሊኖረኝ? ሁሉም ውሸት እንደሆነ ይቅርታን በሚጠይቅ ቅላጼ ነገርኩት፡፡ ምንም ሳይናገረኝ በቆምኩበት ጥሎኝ ሄደ፡፡ ከዚያን ዕለት ጀምሮ ከዶርም መውጣት ጠላሁ፡፡ የባህል ማዕከል ልጆችም ሊያነጋግሩኝ ሁለት ሶስቴ ቢያስጠሩኝም ለማነጋገር አልፈለኩም፡፡ ወይ አርቆ አለማሰብ? የሰውን ስሜት በውሸት ስለጎዳው ጤነኝነት አልተሰማኝም፡፡ በቃ ይህ አይነቱ ጨዋታ ጥሩ አይደለም ብልም ወደኋላ ግን ተመልሶ ማስተካከል ስለሌለው አዘንኩ፡፡ ከዚህ ስሜት ነጻ የምወጣበት ቀን ናፍቆኝ እንሆኝ አለሁ፡፡ በሉ እስቲ በጥሩና በእውነተኛ ስራ ያገኛኘን፡፡ ደህና ሰንብቱ!!



# ከስኬታማ ተማሪዎች አንደበት



ሰለሞን አማረ የኢኮኖሚክስ ት/ክፍል ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.99)

"ዩኒቨርሲቲ ማለት በርካታ ነገሮችን የምትማርበት ትልቅ ተቋም ነው፡፡ ብዙ ሰዎች የቀለም ትምህርት ብቻ የሚሰጥበት ተቋም ይመስላቸዋል፡፡ እውነታው ግን ከቀለም ትምህርት ባሻገር በርካታ ቁም ነገሮችን ተምረህ የምትወጣበት ተቋም ነው፡፡ በእርግጥ እኔ በስራ አለም የተወሰነ ስለቆየሁ የዩኒቨርሲቲ ሕይወትን ለመላመድ ብዙ አልተቸገርኩም በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲ እራስህን ፈልገህ የምታገኝበት ተቋም ነው፡፡"



ትዕግስት ፍቅረማርያም የማኔጅመንት ት/ክፍል ተማሪ

(አማካኝ ውጤት 3.93)

"ይህ ዩኒቨርሲቲ አንጋፋ ነው ለዚያም ነው "Wisdom at the source of Blue Nile" ሲል የሚደመጠው፡፡ ይህ ኃይለ ቃል ሚስጢሩ ጥልቅ ነው፡፡ የዚህን የእውቀት ጥበብን መቅሰም ስለምሻ ነው አንደኛ ምርጫዬ አድርጌ የሞላሁት በምርጫዬም መሰረት ሲደርሰኝ በጣም ነበር የተደሰትኩት፡፡ ምርጫዬ ስህተት አልነበረም በጣም ጥሩ የሆነ እውቀት አስጨብጦኛል፡፡ ከቀለም ትምህርት ባሻገር ጥሩ ማሕበራዊ ኑሮ ፈጥሮልኛል፡፡ ይህም በተለያዩ ክበባትና ማሕበራት መሳተፌ ነው፡፡ ከቀለም ትምህርት ባሻገር ክበባት የወደፊት ራዕያችንን የሚፈነጥቁልን ብርሃናት ናቸው፡፡"

ሜቲ ግዛው የእፅዋት ሳይንስ

ት/ክፍል ተማሪ

(አማካኝ ውጤት 3.92)



"ማንኛውንም ከባድ ነገር ከመሸሽ ይልቅ ለማሸነፍ መጋፈጥ እንዳለብኝ አስባለሁ፡፡ ሁሌም የሰራነው ሁሉ ውጤታማ ይሆናል ብለን ሳይሆን ያሰብነው እስከሚሳካ በትዕግስትና በፅናት መጠበቅ መቻል እንዳለብን አምናለሁ፡፡ ለስኬቴ ትልቁ ሚስጥር ግን እግዚአብሔር ሆኖ በተጨማሪ ቤተሰቦቼ ናቸው፡፡"

◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇



ሂዊ አባራያ የእንስሳት እርባታና ቴክኖሎጂ ት/ክፍል ተማሪ

(አማካኝ ውጤት 3.94)

"መማር ማለት ለእኔ የሚገባኝ ነገሮችን ከተለያዩ አቅጣጫ ማየትና በቀና አመለካከት የተሰጠውን ኃላፊነት መወጣት መቻል ሲሆን የተማረ ሰው ማለት ደግሞ ባለበት ደረጃ ላይ ተጨባጭ ሁኔታ ማሳየት የሚችልና ሌሎችን የሚረዳ ሰው ማለት ነው፡፡"




እያሱ አለፈ የታሪክ ት/ክፍል ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.91)

"መማር ማለት የዲግሪ ወይም የማስተር ሰርተፊኬት ማግኘት ብቻ ሳይሆን የባሕሪ ለውጥ ማምጣትም ነው፡፡ ማለትም ቅንነትን፣ በጐ አሳቢነትና ሰባዊነትን መላበስና ግንዛቤ ማሳደግ ነው፡፡ የተማረ ሰው ማለት ይሄ ነው፡፡"



አያሌው ዓለሙ የአደጋ መከላከልና ዘላቂ ልማት ት/ክፍል ተማሪ

(አማካኝ ውጤት 3.94)

"ለእኔ ትልቅ ሞዴል የምላቸው ቤተሰቦቼ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የትምህርት ፍላጐቴ እንዲዳብር ባያበረታቱኝና ምክራቸውን ባይለግሱኝ ኖሮ የማልማርበት አጋጣሚ ይፈጠር ነበር፡፡"



ናትናኤል ሙሉቀን የኮምፒውቲግና ኤሌክትሪካል ምህንድስና ት/ቤት ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.93)

"እንደ እኔ አመለካከት ፍቅርና ትምህርት ያን ያህል ግንኙነት አላቸው ብዬ አላስብም፡፡ ማንኛውም ተማሪ ጊዜውን በፕሮግራም መጠቀም ከቻለ/ከቻለች ሁለቱን አንድ ላይ ማስኬድ የማይቻልበት ምክንያት አለ ብዬ አላስብም፡፡"



አልጋነሽ ይግዛው የኤሌክትሪካል ምህንድስና ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.56)

"ዩኒቨርሲቲ ለኔ ገሃዳዊ ዓለም የሚመለከትበት (የተመለከትኩበት) የሕይወቴ ዘርፍ ነው፡፡ በእውቀቴ ደረጃ በማሕበራዊ ሕይወትና ራስን ወደ ተሻለ የሕይወት አቅጣጫ ከመቀየር አንፃር ያስተማረኝና ኢትዮጵያዊነትም አጉልቶ ያሳየኝ መንደር ነው፡፡ ከቀለም ትምህርት ባሻገርም ማሕበራዊ ሕይወት፣ ችግርን መረዳትንና ለችግሮች መፍትሄ መፈለጊያ ዘዴዎችንም አሳይቶኛል፡፡"

Congratulations!



# ከስኬታማ ተማሪዎች አንደበት



ሳይንስ ሳኬ የጒልማሶች ትምህርትና የማሕበረሰብ ልማት ት/ክፍል ተማሪ

“የዩኒቨርስቲ ዋና ዓላማ በዋናነት ብቁ ንቁና ለልማት ታታሪ ዜጋን ማፍራት ነው። ይህንን ግብ ዳር ለማድረስም የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ። ለምሳሌ የተሳካ መማር ማስተማር እንዲኖር ተቋሙ ባስቀመጠው ደንብ መገዛት ተገቢ ነው። እኔም ደንቡን አከብራለሁ እንዲሁም እገዛበታለሁ። ምክንያቱም እኔን ትልቅ ሰው ለማድረግ ወይም ነገ ትልቅ ቦታ ለማድረስ የወጣ ደንብ እስከሆነ ድረስ ማክበር ይኖርብኛል። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲ ማለት በመረጃ የተመሰረተ ሀሳብ የሚፈልቅበት፤ ብቃት ያለው ትውልድ የሚቀረጽበት፤ በምክንያትና በህግ የበላይነት የሚያምን ዜጋ የሚሰለጥንበት፤ ለሰው ልጅ አስፈለጊ የሆኑት ዕውቀት የሚገበይበት ማዕከል ነው።”

◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇



ታከለ አበበ የመሬት አስተዳደር ት/ክፍል ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.87)

“እኔ ጊዜያዊ ነገር አያስደስተኝም የሚያስደስተኝ ነገር ቢኖር እናቴ ስትደሰት ማየት ነው ስለዚህም የእኔና የእናቴን ህይወት መቀየር አለብኝ ብዬ ስለማስብ ሊሆን ይችላል። ሌላው ደግሞ የራሴ የሆነ ራዕይ አለኝ፣ እቅድም አለኝ በዕቅዴም ጠንካራ አቋም አለኝ። ነገሮችን በትዕግስት አልፋለሁ። በአጠቃላይ ስኬት የሚገኘው ራዕይ በመሠነቅ፣ ትዕግስተኛ በመሆን እና ጠንካራ ሆኖ በመውጣት ነው። ማለትም “Success”=vision + patient + Strength (ስኬት= ራዕይ + ትዕግስት + ጥንካሬ) የሚል ጠንካራ የህይወት መርህ ስላለኝ ነው ብዬ አስባለሁ።”

◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇




ታሪኩ ታደለ የሕግ ት/ቤት ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.73)

“ዩኒቨርሲቲ ማለት ለእኔ ሁለት ልዩ እና ተፃራሪ የሆነ ጫፎች በአንድ ቦታ እና ህግ ተጠርንፈው የሚገኙበት እና ምን አልባትም ለእያንዳንዱ የህይወት ጉዳይ ዋቢ እና ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችል የመማሪያ ስፍራ ነው። በጣም የሚያስደምመኝ የሰው ልጅ ግኝትም የዩኒቨርሲቲ ሀሳብ ነው። ከሌላ ማህበረሰብ እና ወግ ባህል ከመጣ ሰው ጋር በማስተዋወቅ እና ያለውን ሀገራዊ ነገር በመጋራት ሙሉ ሰው እንድትሆን ያደርጋል። ከዩኒቨርሲቲ ያልተማርኩት ነገር የለም የሚገርመው ከሰዎች መልካም ጐን ብቻ ሳይሆን ከሰዎች ስህተትም መማር መቻልህ ነው። ብዙ በሳልና አስተዋይ ሰዎች አጋጥመውኛል። ምርጥና አሪፍ ከሚባሉ አይነቶችም ብቻ ከዛም ከዛም የሆነ ነገር አይታጣም።”

◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇



ልጃለም መሌ የስታቲስቲክስ ት/ክፍል ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.88)

“ፍቅርና ትምህርት እንደ እኔ ለብቻ ጊዜ እና ቦታ ቢኖራቸው መልካም ነው እላለሁ። ስንቅ ሳይዙ ተጓዥ ማብዛት እንደ ማለት ነው እና ቅድሚያ መስጠት ለሚገባን ቅድሚያ መስጠት አለብን፣ ለሁሉም ጊዜ አለውና።”



ሙሉጌታ ደበበ የስፖርት ሳይንስ ት/ክፍል ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.83)

“ለስኬቴ ምስጢር ደግሞ ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም ያልገባኝን ከመምህሮቼ ጠይቄ ለመረዳት በመሞከርና ሀሳብ ከተማሪዎች ሼር ማድረግ በመቻሌ ነው።”



ስንታየሁ ገብሩ የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽንስ ት/ክፍል ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.92)

“ዩኒቨርሲቲ ለእኔ ሕይወትን አቅርቦ የሚያሳይ መነፅር ነው። ልትጠቀምበት በመትችለው መጠን ልክ የሚጠቅም ነፃ ሜዳ ነው። በአንድ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሆኖ ኢትዮጵያነትን መቃኘት የሚያስችል አቋራጭ የማንነት መለያ ቦታ ነው።”

◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇



እርቂሁን ዘላለም የቴክስታይል ምህንድስ ት/ክፍል ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.79)

“ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት አላማዬ ስለነበር አይሳካልኝም የሚል ሃሳብ አልነበረኝም። አንድ ሰው በዓላማ ይሄን አደርጋለሁ ብሎ ካቀደ እና ለእቅዱ የሚሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ከቻለ ግቡን በአግባቡ ያሳካል። ለተማሪ ደግሞ ዋናው እቅድ በኘሮግራም ማንበብ ሲሆን ይህን አደርግ ስለነበር እወድቃለሁ የሚል ስጋት አልነበረኝም።”

◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇



እንኳን ደስ አላችሁ!

ታደሰ ቀለሙ የሜካኒካል ምህንድስ ተማሪ
(አማካኝ ውጤት 3.92)

“ዩኒቨርሲቲ የመላ የሀገሪቱ ተማሪዎች ከተለያዩ ቦታ ተሰብስበው እውቀት የሚገበዩበት፣ ማሕበራዊ ኑሮ የሚያገኙበት ተቋም ነው። በቆይታዬም ከቀለም እውቀት ማዳበር በተጨማሪ የማሕበራዊ ኑሮን፣ ችግርን እንዴት በመተባበር መፍታት እንደሚቻል፣ ሀላፊነት ያለብኝና መወጣት ግዴታዬ መሆኑን የተማርኩበት ክፍል ነው።”






# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከየት ወደ የት?

## የወፍ በረር ቅኝት

በታድዬ አስማረ

ባሕር ዳር ከተማ በ17ኛ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ እንደተቆረቆረች የተለያዩ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ ከተማዋ በአባይ ወንዝና በጣና ሐይቅ ዳርቻ ትገኛለች፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ስሟም ባሕር ዳር ለመባል በቅቷል፡፡ የሕዝቡ ቁጥር ከ17 ሺህ በላይ ነው፡፡ የአማራ ክልል ዋና ከተማ የሆነችው ባሕር ዳር የተለያዩ ጥንታዊ ቅርሶ የሚገኙባትና ተፈጥሮ የለገሳት ውብና ማራኪ ከተማ ናት፡፡ እንደ ዋና ከተማነቷ የተለያዩ ተቋማት በውስጧ ይዛለች፡፡ ከነዚህም ውስጥ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አንዱ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የተቋቋመ ሲሆን የ52 አመት እድሜ ያስቆጠረ አንጋፋ ተቋም ነው፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የባሕር ዳር ፖሊ ቴክኒክ እና የባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ ተቋማትን በማዋሀድ በ1992 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተቋሙን መርቀው ሲከፍቱና የመጀመሪያ ሰልጣኞችን ሲሸልሙ

## ባሕር ዳር ፖሊቴክኒክ ተቋም

የፖሊቴክኒክ ተቋም ሲመሰረት እንግዲህ እንዲህ ነው፡፡ በ1952 ዓ.ም ነው፡፡ ንጉሱ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ወደ ቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት ይሄዳሉ፡፡ የቀድሞዋ ሶቭየት መሪዎችም ንጉስ ሀገራቸውን ስለጐበኙላቸው ለንጉሳዊ ክብር ምላሽ ሲባል በጀት መድበው የፖሊ ቴክኒክ ኢንስቲትዩት (ተቋም) በባሕር ዳር ከተማ እንዲቋቋም ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ ንጉሱም በተመለሱ በዚሁ ዓመት በንጉሱ አማካኝነት የመሰረት ድንጋይ ተጥሎ ወደ ግንባታ ለመግባት ተችሏል፡፡ የመሰረት ድንጋይ ንጉሱ ባስቀመጡበት ወቅት በሀገራችን ኢንዱስትሪ ለማስፋፋት እና ወደ ዘመናዊነት ለመሸጋገር የተቋሙ መቋቋም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው በወቅቱ መናገራቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ተቋሙ ሲመሰረት እስከ አንድ ሺ ሰልጣኞችን የመቀበል አቅም እንደነበረው በ1955 ዓ.ም ኃይለስላሴ መርቀው በከፈቱበት ወቅት እንደተገለፀ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ መስከረም 18 ቀን 1956 ዓ.ም ተቋሙ ከየሀገሪቱ ሁሉም አቅጣጫ ተማሪዎችን ተቀብሎ ስራውን ጀመረ፡፡ ስራውን ሲጀምር የፖሊ ቴክኒክ ትምህርት ቤት ይባል ነበር፡፡ ወደ ተቁሙ ለመግባት በተቋሙ የሚሰጠውን የመግቢያ ፈተና ያለፉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ስልጠናው በአምስት የቴክኖሎጂ ትምህርት ዓይነት የጀመረ ሲሆን እነሱም በአግሮ ሜካኒክስ፣ በኤሌክትሪካል ምህንድስና፣ በቴክስታይል ቴክኖሎጂ፣ በኢንድስትሪያል ኬሚስትሪ እና በእንጨት ቴክኖሎጂ ነበር፡፡ በጀመረ በስድስት አመቱ በ1962 ላይ የብረታብረት ቴክኒኖሎጂ ስድስተኛው የትምህርት ዘርፍ ተከፈተ፡፡ ለእነዚህ የትምህርት መስኮች የሶቭየት ሕብረት መንግስት የትምህርት ቁሳቁሳቸውን ያሟላ ሲሆን ስርዓተ ትምህርትም በመቅረፅ ሥራውን እንዲጀምር ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ተቋሙ በ20 ኢትዮጵያውያን፣ በ19 ሩሳውያን እና በዘጠኝ ሕንዳውያን ስራውን ሲጀምር በአጠቃላይ በ48 መምህራን እና በ40 የአስተዳደር ሰራተኞች ነበር፡፡

ፓሊቴክኒክ ለመጀመሪያ ጊዜ 237 ሰልጣኞችን ተቀብሎ ስልጠናውን ሲጀምር ሁሉም ሰልጣኞች ስምንተኛ ክፍልን ያጠናቀቁ እና በተቋሙ የሚሰጠውን የመግቢያ ፈተና ያለፉ ነበር፡፡ ነገር ግን ስልጠናውን በትክክል አጠናቀው የወጡ 150 ሰልጣኞች ብቻ ነበሩ፡፡ በቀጣዩ አመት 10ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ተማሪዎችን በመቀበል የስለጠና ጊዜውንም አራት (4) አመት በድረግ እስከ 1961 ዓ.ም አሰልጥኗል፡፡ በመጨረሻም በ1962 ዓ.ም የመጀመሪያ ትምህርት ቤት ደረጃ ስያሜውን ወደ ተቋም ደረጃ (የኢንስቲትዩት) በማሳደግ በመላ ሀገሪቱ የ12ኛ ክፍልን ያጠናቀቁና የቴክኖሎጂ ትምህርት ዝንባሌ ያላቸውን ብቻ በመመልመል የሁለት ዓመት ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ የዲፕሎማ ምሩቅ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ይህ ስልጠናም እስከ 1970 ዓ.ም በመቀጠል ታላላቅ ምሁራንን አፍርቷል፡፡

በ1971 ዓ.ም ሀገሪቱ በምትፈልገው ደረጃ ብቁ ሙያተኞችን ለማፍራት ሲባል የሁለት ዓመት ስልጠና በቂ አለመሆኑ ተገምግሞ የሶስት አመት የስልጠና ጊዜ እንደሆን በማድረግ በከፍተኛ (በአድቫንስ) ዲፕሉማ ደረጃ እንዲያሰለጥን በትምህርት ሚኒስትር ፈቃድ ተሰጦት ማሰለጠን ጀመረ፡፡ ተቋሙ የስልጠና ፈቃድ ሲሰጠው እንዲሁ ሳይሆን የተቋሙ መምህራን በየጊዜው ከሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ስልጠና በመውሰድ እና ሙያቸውን አሳድገው በመገኘታቸው ነበር፡፡ በተለይ ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ ተቋሙን በሀገር በቀል መምህራን ለመተካት በተደረገው ጥረት በርካታ መምህራን ወደ ውጭ ሀገር ሂደው ተምረው ተመልሰዋል፡፡ የተቋሙ የስልጠና አቅምም ከፍተኛ ነበር፡፡

ስለዚህ በተቋሙ ሀገር በቀል ሙሁራን በመበራከታቸው ምክንያት በ1977 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የስርአተ ትምህርት ክለሳ አድርጓል፡፡ ስርአተ ትምህርቱን ለማሻሻል የተሰጠው ምክንያት ሀገራዊ መሰረት እንዲኖረው ለማድረግ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ሀገራዊ መሰረት የያዘ ስርአት ትምህርት በመቅረፅም በተለይ ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ በተማሪዎች የቀረቡ የመመረቂያ ፈጠራ ስራዎቻቸው አይነተኛ ምሳሌ ነበሩ፡፡ በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶችም ተቋሙ ከተመሰረተ አንስቶ በተማሪዎች የተሰሩ በተቋሙ ይገኛሉ፡፡

በተቋሙ ተመርቀው የወጡ ተማሪዎችም በአለም አቀፍ ደረጃ ተፅዕኖ ፈጣሪ ተመራማሪዎች፣ መሃንዲሶችና ሳይንቲስቶች መሆን ችለዋል፡፡ በፖሊ ቴክኒክ ከተሰሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንደ የውሃ ላይ ሳይክል፣ አውቶማቲክ ጠመንጃ፣ ሶስት ሰው የምትይዝ የቤንዚን መኪና፣ ሬዲዮ እና የመሳሰሉት ተሰርተዋል፡፡

ፖሊ ቴክኒክ ከትምህርት ሚኒስቴር የሚመደብለትን ብቻ አልነበረም ተቀብሎ የሚያስተምረው፡፡ በተለይም በ1984 ዓ.ም በማታው መርሃ ግብር ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማሰልጠን በአነስተኛ ክፍያ የባሕር ዳር ከተማና አካባቢዋ ወጣቶች የትምህርት እድል እንዲያገኙ ለማድረግ ችሏል፡፡

በመጨረሻም ፖሊቴክኒክ በከፍተኛ ዲፕሎማ ብቻ ማሰልጠኑ በቂ ባለመሆኑ ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ የዲግሪ ፕሮግራም ጀመረ፡፡ በተጨማሪም አዳዲስ የትምህርት መስኮችን በመክፈቱ የተማሪ ቅበላውም በከፍተኛ ደረጃ ያደገበት ጊዜ ነበር፡፡

## ባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ

በባሕር ዳር ከተማ ሁለተኛ የሆነው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የባሕር ዳር ሙምህራን ኮሌጅ ሲሆን አካዳሚ ኦፍ ፔዳጐጂ ይባል ነበር፡፡ ይህ ተቋም ሲቋቋም በምስራት አፍሪካ ሁለገብ የመምህራን ማሰልጠኛ ለማድረግ ታስቦ የተቋቋመ ነው፡፡ በስልጠና ፕሮግራሙም ብቸኛው ተቋም እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡

ኮሌጁ በ1965 ዓ.ም በኢትዮጵያ መንግስት፣ በዩኒስኮና በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም /ዩ.ኤን.ዲ.ፒ/ በታደገ ስምምነት ተመሰረተ፡፡ ኮሌጁ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንን የሚያስለጥኑ ሁለገብ መምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮችን፣ የአመራር ባለሙያዎችን፣ የጐልማሶች ትምህርት አስተባባሪዎችንና የሕብረተሰብ እድገት ፕሮግራም አስተባባሪዎችን ተቀብሎ መሰልጠን ጀመረ፡፡

ባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ በባሕር ዳር ከተማ እንዲሆን የተደረገው ከለንደን ዩኒቨርሲቲ ጥናቱን እንዲያጠኑ በተላኩ ምሁራን በፕሮፌሰር ሊዊስ እና ተባባሪ የነበሩት ሜስካፕ አማካኝነት በተደረገ የምርት ውጤት ነበር፡፡ ስያሜውንም አካዳሚ ኦፍ ፔዳጐጂ እንዲሆን መሰየማቸውን “ብሉ ቡክ” በተባለ መፃሕፍቸው ላይ እንደሚገኝ ታሪክ ያስረዳል፡፡ የስያሜው መነሻ የሆነው ሁለገብ የሆኑ መምህራን የሚሰለጥኑበት ተቋም እንደሆነ ታሳቢነት ነበር፡፡ የስልጠናው አይነት ደግሞ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በምስራት አፍሪካ ላሉ ሀገራት ጭምር ታሳቢ ያደረገ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡

ኮሌጁ በአንድ አመት ውስጥ በመጠናቀቅ በ1966 ዓ.ም 100 ተማሪዎችን ለማሰልጠን ተቀብሏል፡፡ ነገር ግን ወቅቱ አብዮት የፈነዳበት እና እድገት በሕብረት የታወጀበት ጊዜ ስለነበር ስልጠናው ሳይጀመር የተመደቡት ተማሪዎች ወደ ሀገራዊ ጥሪው እንዲሄዱ በመደረጉ ስልጠናውን ለመጀመር አልተቻለም ነበር፡፡

እንደገና በ1967 ዓ.ም 496 ሰልጣኞችን ለሁለተኛ ጊዜ የተቀበለ ቢሆንም ግዳጁ ሥራው ባለመጠናቀቁ ተማሪዎቹ ወደ ግዳጁ በመሄድ አሁንም ስልጠናው ለመጀመር አልተቻለም፡፡ ኮሌጁ ምንም እንኳ ለሁለት ጊዜ ሰልጣኞችን የተቀበለ ቢሆንም በሁለትም ዙር ከተመደቡት 596 ተማሪዎች መካከል 18 ተማሪዎች ብቻ ወደ ተቋሙ በመመለስ በኮሌጁ የመጀመሪያ ተመራቂዎች ለመሆን ችለዋል፡፡

ወደ ገጽ 16 ዞሯል

Congratulations!



# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ...

ከገጽ 15 የዞረ

በኮሌጁ ይሰጥ የነበረው ስልጠና ፔዳጐጂካል ሳይንስን ሜጀር በማድረግ ማይገር ደግሞ በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በሂሳብና ጂኦግራፉ ትምህርት ዘርፎች አንዱን በማድረግ ሲሰጥ ቆይቷል፡ ፡ ዲግሪውም የሶስት አመት ስልጠና ቢኤዲ (BED) የተባለውን የማስተማር መረጃ ዲግሪ በመስጠት ነበር፡፡ ነገር ግን በ1972 ዓ.ም ከሶስት ዓመት ዲግሪ ስልጠና ፕሮግራም ወደ አራት አመት የስልጠና ፕሮግራም በመቀየር ቢኤ (BA) የተባለ ዲግሪ መስጠት ጀመረ፡ ፡ በዚህ ወቅትም አካዳሚ ኦፍ ፔዳጐጂ የሚለው ወደ ባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ ተባለ፡፡ እንዲሁም በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች የዲፕሎማ ትምህርት ፕሮግራም መስጠት የተጀመረበትም ነበር፡፡ በኮሌጁ ከተለያዩ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ተማሪዎች እየመጡ ይሰለጥኑበት እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡ የቅበላ አቅሙም በከፍተኛ ደረጃ ያደገበት ጊዜ ነበር፡፡ በተጨማሪም በ1975 ዓ.ም ለባሕር ዳር ከተማና አካባቢዋ ትምህርት ፈላጊ ወጣቶች የማታ ትምህርት በመክፈት በቀላል ክፍያ ወጣቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

ኮሌጁ ከ1971 እስከ 1985 ዓ.ም ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥላ ስር በመሆን ሲተዳደር ቆይቷል፡ ፡ መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአዲስ እንዲደራጁ በደንብ ቁጥር 197/86 በተወሰነው መሰረት ተቋማቱ እራሳቸውን ችለው በቦርድ እንዲተዳደሩ ሲደረግ የፖሊ ቴክኒክና የባሕርዳር መምህራን ኮሌጅ በቦርድ እንዲተዳደሩ ተደርጓል፡፡ ተቋማቱ በቦርድ መተዳደራቸው የተቋማቱን የወደፊት የዩኒቨርሲቲ የመሆን ራዕይን እንዲሰንቁ ለማድረግ ታሳቢነት ነው፡፡ በመጨረሻም ሁለቱ አንጋፋ ተቋማት በመዋሀድ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን በባሕር ዳር ከተማፊት ለፊት በ3.5 ኪሎ ሜትር ርቀት እየተያዩ ሊመሰረቱ ችለዋል፡፡

## ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ1992 በኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት በዶ/ር ነጋሶ ገዳዳ አማካኝነት የመሰረት ደንጋይ ዩኒቨርሲቲው ሕጋዊ ሰውነት ሊያገኝ የቻለው በ1992 ዓ.ም በወጣው የነጋሪት ጋዜጣ ላይ 6ኛ ዓመት ቁጥር 12 ታህሳስ 12 ቀን ሲሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 8/1992 ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስትር እንዲሆን በማድረግ ተመሰረተ፡፡ ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው በህጋዊ ሰውነቱ የተለያዩ ተግባራትንና ዓላማዎች እንዲተገብር የተሰጠው ሲሆን የተለያዩ ፋካሊቲዎችንና ኮሌጆች፣ ኢንስቲትዮቶችና ት/ቤቶች እንዲያስፋፋም ጭምር ነው፡፡

በመሆኑም በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እንድአንድ ትምህርት ክፍል የነበሩት በርካታ ትምህርት ክፍሎች ወደ ተቋም ደረጃ እንዲያድጉ ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ በ1995 ዓ.ም የአሁኑ ኮሌጅ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋካልቲ በሚል ተቋቋመ፡፡ እንዲሁም በ1996 የሕግ ትምህርት ክፍል የነበረው ትምህርት ቤት (school) ቤት በመባል ተቋቋመ፡፡ በአጠቃላይ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ ዲፓርትመንቶችን እያስፋፋ የመጣበት ጊዜ ሲሆን ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የትምህርት ክፍሎችን በየዘርፎቻቸው በመለየት እና እንደ ትምህርት አሰጣጥ ስፋታቸው አንፃር ሌሎች ትምህርቶችን የዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ቅርንጫፍ ተቋማት እንዲኖሩት ተደረገ፡፡ ለምሳሌ የፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት የነበረው የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ተባለ፡፡ ሌላው በኢንስትትዩት ደረጃ የተቋቋመው የቴክስታይልና ጋርመንት ትምህርት ክፍል የነበረውም የቴስታይል፣ ፋሽን ዲዛይን ጋርመንት ኤንስቲትዩት ተብሎ ተቋቁሟል፡፡

**እንኳን ደስ አላችሁ!**

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በየጊዜው መስፋፋቱን የቀጠለ ሲሆን በተለይ በሀገሪቱ ደረጃ አዳዲስ የትምህርት ዘርፎችን በመክፈት እና በሀገሪቱ በማስተዋወቅ ረገድ ግንባር ቀደም ነው፡ ፡ በመሆኑም ከኔዘርላንድ መንግስት ጋር በመተባበር የመሬት አስተዳደር ተቋም በመመስረት ተቋሙ የሀገሪቱን የመሬት አስተዳደር ዘመናዊ ለማድረግ ታስቦ በ1996 ዓ.ም በትምህርት ክፍል ደረጃ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩልቲ ስር እንዲሁም ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ተቋም በማደግ ከሕግ ትምህርት ጋር ይባብ ግቢ በመባል ተሰይሟል፡፡

በ1999 ዓ.ም የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተቋቋመ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ 86 ተማሪዎችን በመቀበል በሕክምና ጤና ሳይንስ ማሰልጠን ጀመረ፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው ከተመሰረተበት ከ1992 እስከ 2000 ዓ.ም ዩኒቨርሲቲው ስምንት ፋኩልቲዎችን፣ ኮሌጆችንና ተቋማትን ለመክፈት ተችሏል፡፡ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ እንደ ሀገሪቱ የሰው ኃይል ስልጠና ፋላጐት መሰረት ያደረገ የስልጠና መስክ ትምህርት ክፍሎችን እንደ የስልጠና ዘርፉ ተመሳስሎአቸው በአዲስ መልክ ለማዋቀር በሁለት ኮሌጆች ሶስት ኢንስቲትዩቶች፣ ሶስት ፋኩልቲዎች፣ በሁለት አካዳሚዎችና አንድ ትምህርት ቤት በማቋቋም ግዙፍ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን በቅቷል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ይህን ሁሉ ቅርንጫፍ ተቋማት ሲከፈትና በተለያዩ መስረተ ልማቶችን ሲገነባ የራሱ የሆነ ተልዕኮ በግልፅ አስቀምጦ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ በዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ የሚታወቀውና ለተግባራዊነቱ ቀን ተሌት የሚሰሩለት ራዕይ (ራዕይ ጥበብ 2017) በመሰነቅ ጉዞውን እየቀጠለ ይገኛል፡፡ ራዕይ ጥበብ 2017 ዩኒቨርሲቲውን በአፍሪካ ካሉ 10 ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንዱ የማድረግ ራዕይ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ በጀት በመበጀት እየሰራ ይገኛል፡፡

ይህ ርዕይ ጥበብ ደግሞ ዩኒቨርሲቲው የያዘውን ተልዕኮ ለማሳካት የሚረዳ ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲው ተልዕኮም አገሪቱ የመትፈልገውን በከፍተኛ ደጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በብዛትና በጥራት በማፍራት፣ አገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ የማሕበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለአገራዊ ብሎም ዓለማቀፋዊ እድገት ጉልህ አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲው የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነት አንፃር የትምህርት ፕሮግራሞችን በየጊዜው እያስፋፋና አዳዲስ ፕሮግራሞችን እየከፈተ ይገኛል፡፡ በእሉት ፕሮግራሞች ላይም ዜጐች የትምህርት እድል እንዲያገኙ ለማድረግ የተለያዩ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎችን ከመደበኛ ፕሮግራም በተጨማሪ በርቀት፣ በማታና በክረምት ዜጎች እንዲማሩ በማድረግ ተደራሽነቱን እያረጋገጠ ይገኛል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የምርምር ዩኒቨርሲቲ የሚያደርገውን ተግባር ለመወጣት ከመጀመሪያ ዲግሪ በተጨማሪ 10 በሁለተኛ ዲግሪ 8 በሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞችን በመክፈት ስልጠና እየሰጠ ይገኛል፡፡ በመሆኑም መጀመሪያ ዲግሪን በመደበኛው ፕሮግራም 18787፣ በማታው ፕሮግራም 4481፣ በክረምት ፕሮግራም 3836 በርቀት ፕሮግራም ደግሞ 12157 ሲሆን በአጠቃላይ 39231 ተማሪዎች ናቸው፡፡ በድህረ ምረቃ ደግሞ በመደበኛው ፕሮግራም 1470፣ በማታ 605 በክረምት 3922 በአጠቃላይ 5997 ተማሪዎች እየሰለጠኑ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በቅድመና በድህረ ምረቃ ሁለት ፕሮግራሞች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉት 45228 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ለእነዚህ ስልጠናዎች መሳካት ግንባር ቀደም የሆኑ መምህራን፣ ተመራማሪዎች እና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች አሉት፡ ፡ በዲ.አችዲ. 161 ማስተርስ 694 የመጀመሪያ ዲግሪ 338 ከዲግሪ በታች 156 ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው ወንድ መምህራንና ተመራማሪ 1146 ሲሆን 198 ሴት መምህራንና ተመራማሪ ይገኛሉ፡፡

ዩኒቨርሲቲው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ ሙሁራኖች በምርምር ስራ ላይ ይገኛሉ፡፡ የምርምር ውጤታቸውንም በታዋቂ የምርምር መፅሄቶች (ጆርናሎች) እያሳተሙ ይገኛል፡፡ እነዚህ የምርምር ውጤቶችም ወደ ማሕበረሰቡ ገብተው የማህበረሰቡን ችግር እንዲፈቱ ዩኒቨርሲቲው እየሰራ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በ2007 ዓ.ም የበጀት ዓመት ብቻ ለአንድ ተመራማሪ የፕሮፌሰርነት ማዕረግ የሰጠ ሲሆን ለ11 ደግሞ የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ሰጠቷል፡፡ እንዲሁም ለ14 ምሁራን የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ በመስጠት ዩኒቨርሲቲ ለያዘው ራዕይ መሳካት አይነተኛ መገለጫ ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲው ሶስት የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያላቸው ምሁራን ይገኙበታል፡፡

የምርምር ውጤቶች ወደ ማሕበረሰቡ እንዲገቡ ለማድረግ በቅርቡ ታትሞ የሚወጣውን ጭምሮ ዩኒቨርሲቲው አራት የምርምር መጽሄቶችን (Journals) እያሳተመ ይገኛል፡ ፡ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው የሚያከናውናቸውን ስራዎች በየወሩ በምትታተመው «ናይል ጋዜጣ» እና በአመት ሁለት ጊዜ በሚታተመው «ጥበበ ዓባይ» መጽሄት ለማሕበረሰቡ እያስተዋወቀ ይገኛል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ተልዕኮና ራዕይ እንዲሳካ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ያለው የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኛ ነው፡፡ እነዚህ የአስተዳደር ሰራተኞች 1565 ወንድ ሲሆኑ 2265 ሴቶች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ 3830 የአስተዳደር ሰራተኞችን ለርዕይ ጥበብ እና የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮ ለማሳካት እየተጉ ይገኛል፡፡

የዩኒቨርሲቲው በ52 ዓመት እድሜው በየተቋማቱ የነበሩ ዲኖች በአመራራቸውና ውሳኔ ከጭነታቸው ዩኒቨርሲቲው ለዚህ ትልቅ እድገት መድረስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጋቸው ሁሉም ይስማማበታል፡፡ በተለይ ሁለቱ አንጋፋ ተቋማት ከባዶ ተነስተው ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲን ለመመስረት የበቁት ሲቋቋሙ ጀምሮ ከነበሩ ዲን እና የአስተዳደር አካላት አንስቶ እስከአሁን ባሉት የተለያዩ ፋኩልቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ተቋማት፣ አካዳሚና ት/ቤት ዲንና ዳይሬክተር እንዲሁም የአስተዳደር አካላት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ1992 ዓ.ም ዩኒቨርሲቲ ከሆነ ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ግለሰቦች በፕሬዚዳንትነትና ም/ፕሬዚዳንትነት መርተዋል፡ ፡ በፕሬዚዳንትነት የዩኒቨርሲቲውን ከመሩት ውስጥ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሽመልስ ኃይሌ ከ1992 እስከ 1996 ዓ.ም ሁለተኛው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፀሐይ ጀንበሩ ከ1996-2001 ዓ.ም በመቀጠል ዶ/ር የሽመብራት መርሻ ከ2001-2003 ዓ.ም ሲሆን በአሁኑ ወቅት ላይ የሚገኙት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ከ2003 ጀምሮ በማስተዳደር ላይ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም ዩኒቨርሲቲውን በምክትል ፕሮዚዳንትነት የመሩ አመራሮች እንደ አመራር ለዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ እነሱም የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ሁነው ካገለገሉት ውስጥ በቅደምተከተል አቶ ግዛቸው አዱኛ፣ ፕሮፌሰር ያለው እንዳወቅ፣ ፕሮፌሰር ሙሉጌታ ክብረት፣ ዶ/ር ፍሬው ተገኘ ሲሆኑ አሁን በስራ ላይ የሚገኙት ዩኒቨርሲቲውን ያገለገሉ ዶ/ር ማተቤ ተፈራ ናቸው፡፡ በአስተዳደርና ቢዝነስ ልማት ም/ፕሬዚዳንትነት ደግሞ ዶ/ር ገ/እግዚአብሔር ካህሳዬ፣ ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ፣ አቶ ዘሪሁን መኮንን፣ ዶ/ር ማረው አለሙ፣ ዶ/ር ገብረ እግዚአብሔር ካህሳዬ (ለሁለተኛ ጊዜ) እና አሁን በስራ ላይ የሚገኙት ዶ/ር እያዩ ሞላ እንዲሁም በቅርቡ የቢዝነስና ልማት ራሱን ችሎ በምክትል ፕሬዚዳንት ለተቋቋመው ጽ/ቤት እየመሩ የሚገኙት አቶ መንግስቱ ገብሩ ናቸው፡፡ የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎትን ምክትል ፕሬዚዳንትነት የመሩት ደግሞ ዶ/ር ፍሬው ተገኘ እና በአሁኑ ወቅት ጽ/ቤቱን እየመሩ የሚገኙት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ናቸው፡፡

በተጨማሪ በምክትል ፕሬዚዳንትነት የሚመራው ዩኒቨርሲቲውን ለውስጥና ለውጭው ማሕበረሰብ የገፅታ ግንባታ ስራ እየሰራ የሚገኘው የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክኮሙዩኒኬሽንም/ፕሬዚዳንት ነው፡፡ ይህ ክፍል ለማሕበረሰቡ ስለ ዩኒቨርሲቲው አጠቃላይ እንቅስቃሴ እያስተዋወቀ ይገኛል፡፡ መረጃዎችን የዩኒቨርሲቲው ልሳን በሆነችው «ናይል» ጋዜጣ እና በዩኒቨርሲቲው ድህረ ገፅ መረጃዎችን እያሰራጨ ሲሆን በየጊዜው ብሮሸሮችን፣ ካላንደሮችንና አጀንዳዎችን በማሳተም ለሕብረተሰቡ እንዲዳረሱ በማድረግ ከፍተኛ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡ ክፍሉን በምክትል ፕሬዚዳንትነት እየመሩ ዩኒቨርሲቲውን ለከፍተኛ እውቅና ካበቁት መካከል ዶ/ር ፋንታሁን አየለ፣ አቶ ሞላ አባቡ እና በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ የሚገኙት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ ናቸው፡፡ በጽ/ቤቱ ስር የውስጥና የውጭ ግንኙነት ዳይሬክተሮች አሉት፡፡

አንጋፋ የሆነው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በወፍ በረር ቅኝት ከሞላ ጐደል ይህን ይመስላል፡፡ ቀጣዩ የስራ ዘመንም ጠንክረን በመስራት ራዕይ ጥበብ 2017ን የምናሳካበት ዘመን ይሁን እያልን ለ2007 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪዎች እንኳን ደስ አላችሁ እንላለን፡፡

ቸር ይግጠመን!!!